



# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ

# 6ኛ ክፍል



የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ

እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ


አዘጋጆች፡-ዳንኤል ኃይለ ኢየሱስ (MA)

ህይወት ታምሩ (MA)

ሰለሞን ሰርካ (BA)

ኤዲተር፡- ሃብታሙ መስፍን (MA)

ጥራት ተቆጣጣሪ፡-ዶ/ር እንግዳ ዘውዴ (PHD)

አወቀ ፀጋዬ (MA)



ጥቅምት 2014

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢ.ፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

# የይዘት ማውጫ

ምዕራፍ 1

መረዳዳት ------------------------------------------------------------ 5

ምዕራፍ 2

ባህላዊ የግጭት አፈታት ---------------------------------------------20

ምዕራፍ 3

የሴቶች ሚና ----------------------------------------------------------39

ምዕራፍ 4

ስለ አካባቢ መናገር ------------------------------------------------51

ምዕራፍ 5

የታዋቂ ሰዎች ታሪክ ----------------------------------------------- 62

ምዕራፍ 6

ሀገር ወዳድነት ------------------------------------------------------76

ምዕራፍ 7

ባህል ------------------------------------------------------------------87

ምዕራፍ 8

መቻቻል ---------------------------------------------------------------102

ምዕራፍ 9

ተላላፊ በሽታዎች ----------------------------------------------------111

ምዕራፍ 10

የፈጠራ ስራ -----------------------------------------------------------120

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የ6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ የሚማሩ ተማሪዎች በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መጽሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ፣ ስዋስውና ሥነጽሑፍ በእኩል ደረጃ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስርዓተ ትምህርቱንና እና መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች አካቷል፡፡

1. ተማሪዎች ስዕሎችንና ርዕሶችን በመመልከት የቅድመ ማዳመጥና ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲገምቱ በማድረግ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥና በማንበብ የማዳመጥና የማንበብ፣ የመጻፍና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

2.ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይንም ንባብ በሚገባ በማዳመጥና በማንበብ የአዳምጦ/የአንብቦ መረዳት በንግግርም ሆነ በፅሁፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ በተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡

3.ተማሪዎች ባዳመጡትና ባነበቡት ፅሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንደየአጠያየቃቸው የሚወክሏቸውን ፍቺ በመፃፍ በተገቢው የቃላት አሰዳደር ስርዓት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያለማምዳቸዋል፡፡

4. ተማሪዎች በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሰረቱ ዓረፍተነገሮችን ማንበብ እንዲችሉ ልልምድ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡

5.ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቻቸውን አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያደምጡትንና የሚያነቡትን ሃሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት እውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በፅሁፍ ሃሳባቸውን በአግባቡ እንዲገልጹ ይረዳቸዋል፡፡

6. ተማሪዎች የተለያዩ የሰዋስውና የሥነጽሁፍ ተግባራትን እንዲሰሩና እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል፡፡

**ምዕራፍ አንድ** (9 ክፍለ ጊዜ)

**ርዕስ ፡- መረዳዳት**

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- በመጣመራችው ምክንያት ተጨማሪ ፍች የሚያመጡ ቃላትን ፍች አዳምጠው ይመልሳሉ፡፤
- የሚና ጫወታዎችን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡
- ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን አውቀው ቃላትን በትክክል ያነባሉ፡፡
- ሥርዓተ ነጥቦችን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡
- ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ መሣሪያዎችን ሥም ይዘረዝራሉ፡፤
- ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያን ድህረ ቅጥያን በመነጠል ያወጣሉ፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ**

**ማዳመጥ**

- ቃላት ሲጣመሩና በተናጠል ሲሆኑየሚኖራቸውን የፍች ልዩነት አዳምጠው ይናገራሉ፡፡
- ቃላትን በትክክል ያጣምራሉ፡፡
- **ዝርዝር ይዘቶች**
- **ማዳመጥ**

- የተጣመሩ ቃላትን ማዳመጥ
- የጥምር ቃላትን ፍች መናገር

**ክፍለትምህርት አንድ(ማዳመጥ)** መምህር ተማሪዎች በማስታወሻ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠውን አጭር ማብራሪያ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ምሳሌዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፈው ቃሎቹን እየጠሩ እንዲያዳምጡና ፍቺውን እንዲናገሩ እያደረጉ ያለማምዷቸው፡፡ በመቀጠልም ለክፍል ሥራ የቀረቡትን ቃላት በመጀመሪያ ይጥሩላቸውና አዳምጠው ቀጥተኛ ፍቻቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በመቀጠል ጥምር ቃለቱን ይጥሩላቸው፤ አዳምጠው ፍቺያቸውን ይናገሩ ፡፡

- ማሳሰቢያ- መምህር ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በክፍሉ ውስጥ ካሉ ትምህርቱን ለመከታተል እንዲችሉ እገዛና ድጋፍ እንዲያገኙ ከተማሪዎች ጋር አሰባጥረው ያስቀምጧቸው፡፡

ቃላት

የተለያዩ የአካል ጉዳተኞችን መገልገያ መሣሪያዎች ስሞችን ይዘረዝራሉ፡፡

**ቃላት**

- የአካል ጉዳተኞች መገልገያዎች
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት

**ክፍለ ትምህርት ሁለት (ቃላት)** በስዕሉ ላይ የተቀመጡትን ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡትን መሣሪያዎች ስም እንዲናገሩ ያድርጓቸው ነገር ግን ሥራውን የሚሰሩት በቡድን በመሆን ነው፡፡በመቀጠልም የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

**(ፍንጭ)**መምህር የመገልገያ መሳሪያዎቹን ስም ላያውቁ ስለሚችሉ አካል ጉዳተኞች በአካባቢያቸው የሚጠቀሙባቸውን መገልገያዎች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ስዕሉ ላይ ያሉትን መሣሪያዎች ስም እርሰዎ ይንገሯቸው፡፡

ዊልቸር፣ክራንች፣አርቲፊሻል እግር፣ ስታይለስ/መጻፊያ/፣ ስሌት/ቦርዱ/

**መናገር**

- የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡
- ስለሚወዷቸው ጨዋታዎች ይናገራሉ፡፡
  - አጫጫር ጭውውት ያቀርባሉ፡፡
  - ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን ለቅመው በማውጣት ያሳያሉ፡፡
  - ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን ጠብቀው ያነባሉ፡፡
  - ካነበቡት ምንባብ መረጃ ያወጣሉ፡፡

**መናገር**

- ጭውውት

-የሚና ጫወታ

**ክፍለትምህርት ሶስት (መናገር)** መምህር በቅድሚያ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተራ ይጠይቋቸውና ተማሪዎቹ ጥያቄውን ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት ንግግራቸውን እንዲያዳብሩ ያድርጉ (ሁሉም ተማሪዎች የሚናገሩበትን ዘዴ ይጠቀሙ) በመጨረሻም አንድ ባህላዊ ጨዋታ በመምረጥ አዘጋጅተው አምጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**መፃፍ**

- የሥርአተ ነጥቦችን ምንነት አውቀው ይናገራሉ።
- በአረፍተ ነገር ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን በትክክል ይጠቀማሉ።
- የተጓደሉ ሥርዐተ ነጥቦችን ያሟላሉ።

**መፃፍ**

- ሥርዓተ ነጥቦች
- ሥርዓተ ነጥቦችን ተጠቅሞ መፃፍ

**ስዋሰው**

- ስለቅጥያ ምንነት አውቀው ያብራራሉ።
* ቅድመ ቅጥያን ነጥለው ያወጣሉ።
- ድህረ ቅጥያን ነጥለው ያወጣሉ።

**ሥነ ጽሁፍ**

ስለ እንቆቅልሽ ምንነት አውቀው ይናገራሉ።

እንቆቅልሽ ያቀርባሉ።

**ማንበብ**

- ሳልስና ሳድስ ፊደላት
- ምንባብ
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች

**ሰዋሰው**

- ቅጥያ

ቅድመ ቅጥያና ድህረ ቅጥያ

***ሥነ ጽሁፍ***

- እንቆቅልሽ
- ጥያቄና መልስ

**ክፍለ ትምህርት አራት(ማንበብ)** በመጀመሪያ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን ጽፈው በማሳየት እንዴት እንደሚነበቡ ይንገሯቸው፡፡ ቀጥለው ተማሪዎቹን ያስነብቧቸው፡ ፡ከዚያም በቃል ደረጃ ሳልስና ሳድስን ያስነብቧቸው ቃላቱን በትክክል ካነበቡ በኋላ የተዘጋጀውን አጭር ምንባብ ሳልስና ሳድስን ጠብቀው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

ዘወትር ጧት ከመኝታህ እንደተነሳህ ፊትህን መታጠብ አለብህ፡፡ ቁርስህን ከበላህ በኋላ ጥርስህን መፋቅ አትርሳ ይህም ለንጽህናህ ብቻ ሳይሆን የጥርስህንም ጤንነት ይጠብቅልሃል፡፡ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሁል ጊዜ ንፁህ ሆነህ መታየት አለብህ፡፡ በእረፍት ጊዜህ ደግሞ ልብስ ማጠብና ሌላም ስራ መስራት እንዳለብህ እወቅ፡፡ ጤንነትህ የተጠበቀ እንዲሆን ሁል ጊዜ ንፁህ ልብስ መልበስና ገላህን መታጠብ አለብህ፡፡ በዚህ አይነት ንፁህ ሆነህ የሚያዩህ ሰዎች ሁሉ ጥሩና ጎበዝ ልጅ ነህ ይሉሀል፡፡

ክፍለ ትምህርት አምስት (አንብቦ መረዳት) መምህር በመጀመሪያ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ምንባቡን በግል እንዲያነቡት ያድርጉ ፡፡በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰያድርጉ፡፡ ይህንን ምንባብ ሲያነቡ ቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ የሚለው ዘዴ እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪዎቹን የምንባቡን ጥያቄዎች እራስዎ በቃል ይጠይቋቸው፡ ፡ በጽሁፍ የሚመልሱትን በግል እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

## መስማት የተሳናቸው

አብዛኛውን ጊዜ የመስማት ችግር ያለባቸው ህፃናት የመናገር ችግር አለባቸው፡፡ የንግግር ድምፃቸውንም ሰዎች ሲሰሙት ያልተለመደ አይነት ይመስላል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት መስማት የተሳናቸው ሰዎች የንግግር ድምጽ ምን አይነት ድምጽ ሊኖረው እንደሚችል ስለማያውቁ ነው፡፡ ለእነዚህ ህፃናት በትክክለኛው ቋንቋ መናገር በጣም ይከብዳቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት መስማት መስማት የተሳናቸው ህፃናት አለመናገርን ይመርጣሉ፡፡ እናም በአካላዊ እንቅስቃሴዎች (gestures) ወይም በምልክቶች ብቻ ይግባባሉ፡፡የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች ለመናገር ስለሚፈሩና ስለሚያፍሩ ፣ ለመናገር የሚደፍሩት በደንብ ከሚያወቋቸውና ከሚግባባቸው ሰዎች ጋር ብቻ ነው፡፡ እነዚህ መናገር የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ልዩ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ድጋፉ ደግሞ በማህበራዊ ህይወታቸው ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ትልቅ እገዛ ያደረግላቸዋል እና በምናደርግላቸው ድጋፍና እርዳታ ከእለት ተእለት ህይወታቸው ጀምሮ እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን፣ ችሎታቸውን ፣እንዲያዳብሩ ከፍተኛ እገዛ ያደረግላቸዋል፡፡ መስማት የተሳናቸው ህፃናት በማህበረሰቡ ውስጥ መሳተፍ፣ የሚባለውን መስማት፣ የሚደረገውን ነገር መስማት ይፈልጋሉ፡፡ በነዚህ ሂደቶች ውስጥ ይህንን ለማድረግ ድጋፍና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በትምህርት ቤት ለመማር ሲመጡ ልንረዳቸው ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ህፃናት መስማት የተሳናቸው መሆናቸውን እንዳወቅን ወደ ትምህርት ቤት ሄደው የምልክት ቋንቋ እንዲማሩ በማድረግ ድጋፍ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡ በተመሳሳይም ወላጆቻቸውም ሆኑ ተመሳሳይ ሰዎች በምልክት ቋንቋ በመማር የሚነገሩ ነገሮችን በመተርጎምና በምልክት ቋንቋ ለነሱ በማስረዳት ሊተረጉሙላቸው ይገባል፡፡

ባጠቃላይ መስማት የተሳናቸው ህፃናት እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሊያውቁ ፣ ሊማሩ ትልቅ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው የእኛ ድጋፍና እርዳታ ሲታከልበት መሆኑን መዘንጋት አይኖርብንም፡፡ መስማት የተሳናቸው ህፃናት በቃ፣ አለቀላቸው ተብለው የሚተዉ አለመሆናቸውን

አውቀን አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ሁሉ በቅንነትና በታማኝነት ልናደርግላቸው ይገባል፡፡

(መስማት የተሳናቸውና ችሎታቸው ገጽ 147 ተሻሽሎ የተወሰደ )

**ተግባር 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የመስማት ችግር ያለባቸው ህፃናት የመናገር ችግር የሚገጥማቸው ለምንድነው ?
2. መናገርና መስማት የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ምን አይነት ድጋፍ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል?
3. መስማት የተሳናቸውና መናገር የማይችሉ ህፃናት መስማት ፣መናገር ከሚችሉ ህፃናት ጋር ባንድ ላይ እንደ ጓደኛ እንዲሆኑ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

**ተግባር 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

ሀ/ መስማት የተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ድጋፍ አይፈልጉም፡፡

ለ/ መስማት የተሳናቸው ህፃናትን መርዳት ተገቢ ነው ፡፡

ሐ/ ብዙን ጊዜ የመስማት ችግር ያለባቸው ሕጻናት የመናገር ችግር የለባቸውም፡፡

መ/ መስማትና መናገር የማይችሉ ህፃናትን ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ አያስፈልግም፡

ሠ/ መስማትና መናገር የማይችሉ ህፃናት ተምረው ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ተግባር 3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተስማሚውንመልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. መስማትና መናገር የተሳናቸውን ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት የምንልከው ለምንድነው?

   ሀ/ ተምረው በምልክት ቋንቋ መግባባት እንዲችሉ፡፡

   ለ/ በተማሩት ልክ እራሳቸውንና አገራቸውን መርዳት እንዲችሉ፡፡

   ሐ/ በራስ የመተማመን ስሜት እዲኖራቸው ለማድረግ ፡፡

   መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

2. መስማት የተሳናቸውና መናገር የማይችሉ ህፃናት ባለ መማራቸው ሊያጡት የሚችሉት ነገር ምንድነው?

   ሀ/ እንደማንኛውም ማህረሰብ ሊያውቁ የሚገባቸውን ነገር ሳያውቁ ይቀራሉ፡፡

   ለ/ እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሊረዱ የሚገባቸውን ነገር ሳይራዱ ይቀራሉ፡፡

   ሐ/ እራሳቸውን ከማህበረሰቡ ዝቅ አድርገው ያያሉ፡፡

   መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

3. መስማት የተሳናቸው ህፃናት አለመናገርን የሚመርጡት ለምንድነው?

   ሀ/ የንግግር ድምጾችን ለይተው ስለማያውቁ ነው፡፡

   ለ/ በትክክለኛው ቋንቋ መናገር ስለሚችሉ ነው፡፡

   ሐ/ በቀላሉ ከጓደኞቻቸው ጋር መግባባት ስለሚችሉ ነው፡፡

   መ/ መልሱ አልተሰጠም፡፡

4. መስማት ለተሳናቸው ህፃናት ከማህበረሰቡ ልዩ ድጋፍ ሲደረግላቸው

   ሀ/ በማህበራዊ ህይወታቸው ደስተኛ እንደሆኑ ያደርጋቸዋል ፡፡

   ለ/ ህይወታቸውን ደስተኛ በሆነ መንገድ መምራት ይችላሉ፡፡

   ሐ/ ተስፋቸውን ያሳድግላቸዋል፡፡

   መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል፡፡

ተማሪዎችን በመጀመሪያ በጥንድ በጥንድ ያድርጓቸው ከዚያም የቀረበውን ተግባር እንዲሰሩና እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ በመጨረሻም ለአጠቃላይ ግንዛቤ መልሱን አብረው ይስሩ፡፡

**ክፍል 6( መፃፍ)** መምህር ስለ ስርዓተ ነጥቦች የቀረበውን ማስታወሻ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምሳሌውን እንዴት እንደተሰራ ያሳዩአቸው፡፡ቀጥለውም በጥንድ የክፍል ስራውን እንዲሰሩ ያድርጉ፤.በመጨረሻም ቀሪውን ተግባር በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ (መምህር በተግባር 3 ላይ በቀርበው ምንባብ ውስጥ የተጓደሉትን ሥርዓተ ነጥቦች በግላቸው እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡)

**አንብቦ መረዳት( 7)** ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ምንባቡን በጥንድ በመሆን እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ከምንባቡ የወጣውን ጥያቄ በቃል እንዲመልሱ ካደረጉ በኋላ ሌላውን ጥያቄ በግል እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ትንሿ ዛይሴ

ዛይሴ የምትኖረው በደቡብ ክልል ውስጥ በምትገኘው ትንሽ ከተማ ዘምሳ ሲሆን ከተወለደች ጀምሮ ማየት አትችልም ነበር፡፡በዚህ ምክንያት ቤተሰቦቿም ስለሷ ይጨነቁ ነበር፡፡ዛይሴ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ እድሜዋ 12 ዓመት ደርሷል፡፡ ምክንያቱም የአካባቢው ማህበረሰብ ማየት የተሳናቸው ልጆች ትምህርት ቤት ገብተው መማር እንደሚችሉ አያወቁም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በዘምሳ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች የአንድ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆነው **ዶቢር** ወደነ ዛይሴ ቤት በመምጣት ከወላጆቿ ጋር ተገናኝና ዛይሴ ወደ ትምህርት ቤት መግባትና መማር እንደምትችልና ተምራም ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደምትችል እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ለዛይሴ መማሪያና መፃፊያ የሚሆን መሳሪያ እንደሚያዘጋጅላትም በመግለጽ በሳምንቱ መጀመሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዘዋት እንዲመጡ ነገራቸው፡፡

ወላጆቿም በጣም ተደስተው ዛይሴን በሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ ወደ ትምህርት ቤት ይዘዋት ሄዱ፡፡ርዕሰ መምህሩም ተማሪዋን ተቀብሎ ወደ አንደኛ ክፍል በመውሰድ ከአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር አስተዋውቋት ተማሪዎቹንም እንዲንከባከቧትና እንዲደግፏት ነገሯቸው ቦታ ካሲያዛት በኋላ ለክፍሉ አለቃ አደራ ብሎት ሄደ፡፡ ዛይሴ በዚያ ቀን በህይወቷ የማትረሳው ከፍተኛ ደስታ ተሰማት፡፡ያገኘቻቸው ተማሪዎች ጓደኛ በመሆን ተራ በተራ ይዘዋት ሲሄዱ ግቢውን ሲያስጎበኟት ፣ከልጆች ጋር ሲያስተዋውቋት ሂሊናዋ በደስታ ተውጦ ጓደኞቿን በጣም አመሰገነቻቸው፡፡እነሱም ሁል ጊዜ ከሷ እንደማይለይዋት፤ እንደሚረዷት፤ አብረዋትም ሁሉን እንደሚያደረጉ ነግረዋት ሲደወል ወደ ቤት አድርሰዋት ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

(ለማስተማሪያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ )

**ተግባር2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ዛይሴ የምትኖረው ምን በምትባል ከተማ ውስጥ ነው?
2. ትምህርት መማር እንዳለባት ለወላጆቿ የነገረው ማነው?
3. ዛይሴ ጓደኞቿን ያመሰገነችው ለምንድነው?

**ተግባር3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ዛይሴ ከመጀመሪያውም ትምህርት ቤት ያልገባችው መማር ስለማትፈልግ ነበር፡፡
2. ዛይሴን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ይዟት የመጣው የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ነው፡፡
3. ዛይሴ ማየት ስለማትችል ወላጆቿ ስለሷ ሁሌም ይጨነቁ ነበር፡፡

4. ማየት የተሳናቸው ልጆች ከሌሎች ልጆች ጋር እኩል የመማር መብት አላቸው፡፡
5. ዛይሴ የተዋወቀቻቸው ልጆች ተራ በተራ ጊቢውን ያስጎበኛት ነበር፡፡

**ተግባር4. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ አገባብ መሰረት በማድረግ ፍች ስጧቸው፡፡**

ሀ/ ተደሰተች　　መ/ ተራ በተራ

ለ/ በህይወቷ　　ሠ/ መማሪያ

**ክፍለ ትምህርት ስምንት ( ሰዋሰው )** ማስታወሻውን ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፤ ቀጥለውም ስለ ቅጥያ የቀረበውን ይዘት ያብራሩላቸው ፣ምሳሌውንም ግለጽ ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ (ሥነ ጽሁፍ)** -በመጀመሪያ ስለ እንቆቅልሽ ምንነትና ጨዋታ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም የተናገሩትን ከማስታወሻው ጋር እንዲያገናዝቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በመፅሐፉ ላይ ያለውን እንቆቅልሽ እንዲሰሩ ያድርጓቸውና እንዴት እንደሚሰሩ ያሳዩዋቸው፡፡

የምዕራፉ ማጠቃለያ ላይ ያለውን ማስታወሻ ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉና በመቀጠልም ጥያቄዎቹን እንዲስሩ ያድርጉ፡፡

**መርጃ መሣሪያ**

- ጌታሁን አማረ (1989) የአማርኛ ሰዋሰው መጽሐፍ
- ከይዘቱ ጋር የሚመጣሙ ስዕሎች፡፡

**ግምገማ**

የቃል ጥያቄዎች በመጠየቅ፤

ተማሪዎች የሚሰሩትን በመመልከት፤

የጽሁፍ ፈተና  በመስጠት፣

አጭር ፈተና በመስጠት ፣

የተግባር ስራ (ቅጥያዎችን እንዲሰሩ ማድረግ)፤

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**የጎደሉትን ስርዓተ ነጥቦች አሟሉ።**

1. ነጠላ ሰረዝና አራት ነጥብ
2. ጥያቄ ምልክት
3. ነጠላ ሰረዝና አራት ነጥብ
4. አራት ነጥብ
5. አራት ነጥብ
6. ጥያቄ ምልክት

**ክፍለ ትምህርት ስምንት**

| ቃል | ዋና ቃል | ቅድመ ቅጥያ | የድህረ ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1.ቤቶች | ቤት | - | -ኦች |
| 2 ከፊታችን | ፊት | ከ - | - ኣችን |
| 3.ተራመደች | - | | - ኧች |
| 1. አሰለጠነ | ሰለጠነ | - አስ | - |

## ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

### እንቆቅልሾች

1.አልጋ

2.አይን

3.ምላስ

4.ፀጉር

## ምዕራፍ ሁለት_ (9 ክፍለጊዜ)

### ባሕላዊ የግጭት አፈታት

1.**የምዕራፉ አላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፦

- የጓደኞቻቸውን ሃሳብ አዳምጠው ይናገራሉ፡፡
- በሚሰጣቸው ርዕስ ላይ የቡድን ውይይት ያደርጋሉ፡፡
- መመሪያዎችን አንብበው ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- በየባህሉ ያሉ ባህላዊ እሴቶች የሚጠሩበትን ስያሜ መዝግበው ያቀርባሉ፡፡
- ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽን በቀላል ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያዋቅራሉ፡፡
- ቀለል ያሉ ታሪኮችን አንብበው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

#### ክፍለ ትምህርት አንድ፡- ቃላት

- የቃላትን ፍች ይናገራሉ፡፡
- ባህል ነክ ቃላትን በዐውዳቸው ይጠቀማሉ፡፡
- ለቃላት ከአውዳቸው አንጻር ፍች ይሰጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት፡- ሥዕልን ተመልክቶ ገለጻ ማድረግ**

- ስዕሎችን ተመልክተው ገለጻ ያደርጋሉ፡፡
- ስዕሎችን ያወዳድራሉ፡፡
- ስዕሎችን በማነጻጸር ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት፡- ማዳመጥ**

- የጓደኞቻቸውን ሃሳብ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፡፡
- በጥንድ በመሆን ንግግሮችን በማዳመጥ መልሰው ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት፡- ማንበብ**

- ምንባቡን በትክክል ያነባሉ
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በትክክል ይሰራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት፡-አንብቦ መረዳት**

- የሚቀርብላቸውን መመሪያ አንብበው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- ትዕዛዞችን አንብበው ይፈጽማሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡- መጻፍ**

- አያያዥ ቃላትን በትክክል ያውቃሉ፡፡
- ነጠላ አረፍተ ነገሮችን በአያያዥ ቃላት ያጣምራሉ፡፡
- ስለ አንቀጽ ምንነት አውቀው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡- ሰዋሰው**

- ባለቤትና ተሳቢን ከዐረፍተ ነገር ውስጥ ያውጣሉ፡፡
- በዐረፍተነገር ውስጥ ማሰሪያ አንቀጽ ይጠቀማሉ፡፡
- ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅመው አረፍተ ነገር ያዋቅራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት፡- መናገር**

- በቡድን ውይይት ያደርጋሉ፡፡
- ውይይቶችን በንግግር ያቀርባሉ፡፡
- የተለያዩ ንግግሮችን ያቀርባሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡- ስነ- ጽሁፍ**

- አፈታሪኮችን ፈልገው በማደራጀት ለክፍል ያቀርባሉ፡፡
- ታሪኮችን ለክፍል ጓደኞቻቸው ይናገራሉ፡

## ዝርዝር ይዘቶች

. **ቃላት**

-የቃላት ፍች

-ባህል ነክ ቃላት

. **ሥዕልን ተመልክቶ ገለጻ ማድረግ**

-ሥዕልን ተመልክቶ መግለጽ

- ስዕሎችን ማወዳደርና ማነጻጸር

**ማዳመጥ**

-የአቻ ንግግር

- ሀሳብን ለጓደኛ መግለጽ

**ማንበብ**

-ምንባብ

- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ

. **አንብቦ መረዳት**

-መመሪያዎችን አንብቦ መተግበር

-ትዕዛዞችን አንብቦ መፈፀም

**መጻፍ**

-አያያዥ ቃላት

-ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ማያያዝ

-አንቀጽ

**ሰዋሰው**

-ባለቤት

-ተሳቢ

-ማሠሪያ አንቀጽ

**መናገር**

-የቡድን ውይይት

-ንግግር ማቅረብ

**ሥነ - ጽሁፍ**

-አፈ-ታሪክ

ታሪኮች

## 2.የትምህርቱ አቀራረብ

**ክፍለ ትምህርት አንድ፡-** (ቃላት) መምህር የቃላትን ፍች ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎችዎ የምዕራፉን አላማ አንብበው እንዲረዱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡ የቃላትን ፍች ሲያሰሯቸው ተማሪዎች ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚገልጹ ቃላትን እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ ጥያቄዎቹን ከመስራታቸው በፊት ስለ አሰራሩ ጥቂት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠት የሚለውን መልመጃ ምሳሌ በመስጠት ግልጽ ያድርጉላቸውና ያፅፏቸው፡፡( ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉላቸው፡፡)

**ክፍለ ትምህርት ሁለት፡-( ስዕልን ተመልክቶ ገለጻ ማድረግ)መምህር** በተማሪው መማሪያ ላይ የተመረጠ ስዕል ቀርቧል፡፡ ስዕሉን ተመልክተው እንዴት ገለጻ ማድረግ እንዳለባቸው አጠር አድርገው ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ስዕሉን ተመልክተው የሚያገኙትን ሀሳብ እስኪያደራጁ ድረስ ማድረግ የሚገባቸውን ተግባራት ይንገሯቸው፡፡ ይኸንን ተግባር ሲያከናውኑ ተማሪዎች ንቁ ሆነው እንዲሳተፉ የራስዎን የማነቃቂያ ዘዴ ይጠቀሙ፡፡

### ኡፋይሴና ሉፓክ

ኡፋይሴና ሉፓክ በአንድ ላይ የሚኖሩ ባልና ሚስት ናቸው፡፡ሁለቱም በቤታቸው ውስጥ ተሳስበውና ተጋግዘው በፍቅር ይኖራሉ፡፡ በሁለቱም መካከል ያለው የሥራ ሁኔታ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ምክንያቱም ማንኛውንም ስራ ሁለቱም ይሰራሉ፡፡ ኡፋይሴ እህል ስትፈጭ ወይም በቆሎ ስትወቅጥ ሉፓክ ወጥ ይሰራል፡፡ ወይም ሉፓክ እንጀራ ሲጋግር ኡፋይሴ ላሞችን ታልባለች፡፡አስፈላጊ ከሆነም ከብቶችን ወደ ወንዝ ይዛ በመሄድ ውሃ ታጠጣለች፡፡ በሉፓክ እና በኡፋይሴ መካከል ይሄ የሴት ነው ፣ ይሄ የወንድ ነው የሚል ምንም አይነት የሥራ ክፍፍልና የሥራ ንቀት የለም፡፡ ሁለቱም የደረሱበትን ሥራ ሁሉ ይሰራሉ፣ ይተጋገዛሉ፣ ይረዳዳሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ደስተኞች ናቸው፡፡

1. ከላይ የቀረበው አጭር ታሪክ ከየትኛው ስዕል ጋር ይመሳሰላል ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ኡፋይሴና ሉፓክን ደስተኛ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው ?
3. ኡፋይሴና ሉፓክ ሁሉንም ስራ በመስራታቸው ባህላዊ ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ ?
4. ባህላዊውን ተጽእኖ ለማለፍና ሌላውን ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**ተግባር3 ከላይ በተማራችሁት መሠረት በቡድን በመሆን ስለ አንድ ቤተሰብ የሥራ ሁኔታ ጽፋችሁ በማምጣት ለክፍል አቅርቡ፡፡**

**<u>ክፍለ ትምህርት ሦስት፡-</u> (ማዳመጥ)፦** ለማዳመጥ በተመረጠው ርዕስ ላይ የአቻ ንግግር እንዲያደርጉ የሚለማመዱበት ምሳሌ ቀርቧል፡፡ የአቻ ንግግሩን ከመለማመዳቸው በፊት የአቻ ንግግር ምን ማለት እንደሆነና እንዴት መቅረብ እንዳለበት አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጧቸው፣፡ የአቻ ንግግር ለማድረግ የሚያግዛቸውን ሃሳብ ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይንገሯቸውና የአቻ ንግግር በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚፈጀውን ጊዜ ይወስኑላቸው፡፡ ይኽንን ተግባር እንዲያከናውኑ ሲያደርጉ ተማሪዎችዎ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የራስዎን የማነቃቂያ ዘዴ ቢጠቀሙ የተሻለ ነው፡፡ በዚሁ ክፍል እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ምሳሌ በመስጠት ቢያለማምዷቸው መልካም ነው፡፡

**የተማሪዎች ቃለ ምልልስ**

አርሳሌ - እንተዋወቅ ማነው ስምህ ?

ቦርድሎ - ቦርድሎ እባላለሁ አንቺስ ?

አርሳሌ - እኔ አርሳሌ እባላለሁ ።

ቦርድሎ - ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል።

አርሳሌ - እኔም ደስ ብሎኛል።

ቦርድሎ - ወዴት እየሄድሽ ነው ?

አርሳሌ - ወደ ትምህርት ቤት

ቦርድሎ - ስንተኛ ክፍል ነሽ ?

አርሳሌ - ስድስተኛ ክፍል ነኝ ።

ቦርድሎ - በጣም ይገርማል ! እኔም የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። በትምህርቴ ደግሞ ጎበዝ ስለሆንኩ የደረጃ ተሸላሚ ነኝ።

አርሳሌ - በጣም ደስ ይላል።

ቦርድሎ - አንቺስ በትምህርትህሽ እንዴት ነሽ?

አርሳሌ - በጣም ጎበዝ ተማሪ ባልባልም መሀከለኛ ተማሪ ነኝ።

ቦርድሎ - ጥሩ ጎበዝ ለመሆን በርትተህሽ ማጥናት ይጠበቅብሻል።

አርሳሌ - ከዚህ በኋላ እኔም ጊዜ በመስጠት በሚገባ ለማጥናት ወደ ፊት ለመሆን የምፈልገውን ለማሳካት እጥራለሁ።

ቦርድሎ - በጣም ጥሩ ውሳኔ ነው የወሰንሽው ሁለታችንም በዚህ ዓመት ተሸላሚ እንደምንሆንተስፋ አደርጋለሁ።

አርሳሌ - እኔም ተስፋ አደርጋለሁ።

ቦርድሎ - በድጋሚ ስለተዋወቅን ደስ ብሎኛል መልካም የትምህርት ጊዜ ይሁንልሽ።

አርሳሌ - ላንተም፣ ቸር ያገናኘን።

ተግባር2. **ከላይ የቀረበውን የተማሪዎች ቃለ ምልልስ ባዳመጣችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

ሀ/ ሁለቱ ተማሪዎች ማና ማን ነበሩ ?

ለ/ ተማሪዎቹ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው?

ሐ/ በትምህርት ጎበዝና ተሸላሚ የነበረው የትኛው ተማሪ ነው?

መ/ ተማሪዎቹ ከምን ጀምረው እስከ ምን ድረስ እንደተነጋገሩ በቅደም ተከተል እየተነሳችሁ ለክፍል ተናገሩ።

ማስታወሻ

እራሳችሁን ለክፍል ተማሪዎች በምታስተዋውቁበት ጊዜ የሚከተለውን ሂደት መጠበቅ ይኖርባችኋል።

- ስማችሁን ከነ አባታችሁ መናገር
- እድሜያችሁን
- የመጣችሁበትን አካባቢ
- የክፍል ደረጃችሁን
- የምትወዱትን የትምህርት ዓይነት
- ወደ ፊት መሆን የምትፈልጉትን
- ወዘተ ….

**ተግባር3. ከላይ የቀረበውን እራስን የማስተዋወቅ ቅድም ተከተል በመከተል መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ተግባር መሠረት እራሳችሁን ለክፍል አስተዋውቁ። በመቀጠልም ቀጥለው በቀረቡት ጥያቄዎች እራሳችሁን ገምግሙ።**

ሀ/ በተማሪዎች ፊት ስቆም ፍርሃት ተሰምቶኝ ነበር?

ለ/ እራሴን ያስተዋወኩት ምንም ሳልጨነቅ ነበር ?

ሐ/ ሳልናገር ያለፍኩት ነገር ነበር?

መ/ በአጠቃላይ አቀራረቤን ስመለከተው መልካም ነበር?

**ክፍለ ትምህርት አራት (ማንበብ ):-** ለማንበብ የቀረበውን ምንባብ ከማስነበብዎ በፊት ተማሪዎች የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ምንባቡን በየግላቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው። ምንባቡን አንብበው ሲጨርሱ የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን እንዲሰሩና የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጭት ማለት ምን ማለት ነው ?
2. ግጭት የሚፈጠረው በምን ምክንያት ነው ?
3. ግጭትን እንዴት መፍታት ይቻላል?

## የጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት

የጋሞ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የግጭት አፈታት ስልት እንዳለው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡በግለሰቦች ይሁን በቡድኖች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በውይይት መፍታትና በሰላም አብሮ ተቻችሎ መኖር ጋሞዎች ካሏቸው እሴቶች አንዱና ዋናው ነው፡፡ የጋሞ የሀገር ሽማግሌዎች እንኳን በትናንሽ ችግሮች ላይ እና በከፍተኛ ሁኔታ በአገር ደረጃ የሚከሰት ችግር እንኳን ቢኖር የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ትልቁ ሚናቸው መሆኑን የውጪ ፀሐፊዎችም ጽፈውላቸዋል፡፡Boeg (2006) እና Freeman (2002) እንደሚገልጹት በጋሞ አካባቢ ያሉ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ብዙ ጊዜ በሀገሪቱ የመንግስት ለውጥ በተደረገበት ወቅት የተፈጠረውን ክፍተት በመሙላት የአካባቢውን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ሂደት ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳደረጉ ይገልፃሉ፡፡

በጋሞ ብሔረሰብ ዘንድ አብዛኞቹ ግጭቶች በባህላዊ መንገድ የሚፈቱ ሲሆን ፣ብዙውን ጊዜ በአፈታት ሂደት ላይ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ በጋሞ ብሔረሰብ ሽማግሌዎች ስለሚከበሩ እነሱ የሚናገሯቸው ቃላቶች ይጠበቃሉ፣ የሚያዟቸው ትዕዛዞች ይፈጽማሉ ፣ የሚወሰኑአቸውም ውሳኔዎች ይፀናሉ፡፡

በጋሞዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ችግር ቢከሰት ለምሳሌ ህይወት የሚያጠፋ ፣ ንብረት የሚያወድም ፣ህብረተሰቡን የሚያፈናቅል ፣ወዘተ ግጭት ቢከሰት ሽማግሌዎች ምንም ለህይወታቸው ሳይፈሩ እርጥብ ሣር በእጃቸው ጨብጠው ፈጥነው ከግጭቱ መሀል ይገባሉ፡፡በመሀከልም ሆነው ተው እኛ ሽማግሌዎች

በመኃል ገብተናል ይላሉ፡፡ማንም ቃላቸውን የሚጥስ የለም ፤ሁሉም ግጭቱን ወዲያው ያቆማል፡፡ሽማግሌዎች ሲናገሩ አንበሳ እንኳን ቢመጣ ሽማግሌዎች እርጥብ ሣር ይዘው ከለመኑት ይቆማል ፤ ወይም ይመለሳል እንጂ አንዳች ጉዳት አያደርስም ይላሉ፡፡በዚሁ መሰረት ነገሩ በሰላማዊ መንገድ በሽምግልና ተይዞ እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ በቅርብ ጊዜ በአርባ ምንጭ ከተማ ላይ የታየው የዚሁ ባህል አንድ መገለጫ ነው፡፡

(የጋሞ፣ የጎፋ ፣የኦይዳ፣ የዘይሴ እና የጊዴቾ ብሔረሰቦች የግልና የጋራ እሴቶች 2008 ተሻሽሎ የቀረበ)

ተግባር1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ በቃል መልሱ፡

1. ግጭትን በባህላዊ መንገድ ለሽማግሌዎች ሰጥቶ መፍታት ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?

2. በጋሞ ብሔረሰብ የሽማግሌዎችን ቃል ማክበርና የወሰኑትን ውሳኔ መቀበል ለአሁነ ትውልድ ምንን ያስተምራል ትላላችሁ?

3. ግጭቶችን ሁሉ ወደ ፖሊስ ጣቢያና ወደፍርድ ቤት ይዞ ከመሮጥ ያለምንም ድካምና ልፋት በአካባቢው ሽማግሌዎች ነገሩን እዚያው መፍታት ጥሩ ነው ትላላችሁ?

4. ግጭት እንዳይከሰት ቀድሞ መሰራት ያለበት ነገር ምንድነው ትላላችሁ?

5. የጋሞ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ሰርአት እንዴት ተወዳጅ ሊሆን ቻለ?

6. ብዙ ብሔረሰቦች የግጭት አፈታት ስርአት ቢኖራቸውም የሽማግሌዎቹን ቃል ተተኪው ትውልድ ስለማይሰማና የወሰኑትን ውሳኔ ስለማያከብር እነዚህ ባህላዊ ዕሴቶች እየቀሩ ሄደዋል፡፡እነዚህን ዕሴቶች ወደ ቦታቸው ለመመለስ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ተግባር2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጠው አማራጭ ትክክለኛውን መልሰ በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት

ሀ/ በሰላም ለመኖር ይረዳል፡፡

ለ/ አብሮ ተቻችሎ ለመኖር ይረዳል፡፡

ሐ/ያስተዳደር ችግር ክፍተቶችን ይሞላል፡፡

መ/ ሁሉም መልስ ነው፡፡

2. በጋሞ ብሔረሰብ ውስጥ ግጭትን በባህላዊ መንገድ በመፍታት ዙሪያ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት------------- ናቸው፡፡

ሀ/ ወጣቶች ለ/ ሴቶች ሐ/ ወንዶች መ/ ያገር ሽማግሌዎች

3. የጋሞ ያገር ሽማግሌዎች ግጭትን ለማብረድ በግጭት መሀከል ሲገቡ የሚይዙት ነገር ----------- ይባላል፡፡

ሀ/ መሣሪያ ለ/ እርጥብ ሣር ሐ/ጦርና ቀስት መ/ሁሉም

4. ሽማግሌዎች የት ሆነው ነው ግጭትን የሚያበርዱት?

ሀ/ በቤታቸው በመሆን ለ/ በሽምግልና ቦታ ተቀምጠው

ሐ/ በግጭቱ መሀል ገብተው

መ/ ግጭቱን በመሣሪያ አስቁመው

5. ከጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት ምን እንማራለን?

ሀ. መከባበርን ለ/ የራስ ችግርን በራስ መፍታትን

ሐ/ ችግሮችን ሳይባባሱ በአጭር ማስቀረትን መ/ ሁሉምመልስ ነው

ከላይ የቀረበውን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ አንብባችኋል፣ እናንተ ደግሞ ከዚሁ ባህላዊ የግጭት አፈታት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት አፈላልጋችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አምጥታችሁ አንብቡላቸው፡፡

ተግባር3 ቀጥለው የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ በምንባቡ መሰረት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ ችግር | ሐ/ ስልት | ሠ/ ደህንነት |
| ለ/ እርጥብ ሳር | መ/ ግጭት | ረ/ ሽማግሌዎች |

**ክፍለ ትምህርት አምስት፡-** (የአንብቦ መረዳት) መመሪያዎችን ሲያሰሯቸው ተማሪዎቹ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አንብበው እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ምሳሌ በመስጠት ግልፅ ያድርጉላቸውና ያሰሯቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡-** (መፃፍ) የአያያዥ ቃላትን መልመጃ ከማሰራትዎ በፊት ስለአያያዥ ቃላት አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ሀረግን ከሀረግ ፣እንዲሁም አረፍተ ነገርን ከአረፍተ፣ ነገር እንዴት እንደሚያይዙ መጠነኛ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ምሳሌዎችንም በመጠቀም መልመጃዎችን እንዴት መስራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡-** (**ስዋስው**) በሚለው ክፍል ስለባለቤት ስለተሳቢና ስለ ማሰሪያ አንቀጽ የቀረበውን ማስታወሻ እንዲያነቡ ያድርጉ ከዚያም የቀረበውን የክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጓቸው ፡፡በተሰጣቸው ርዕስ ላይ በትክክል መወያየት አለመወያየታቸውን ይከታተሉአቸው፡፡

ክፍለ ትምህርት ስምንት (መናገር ) መምህር በተማሪው መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ስዕል ተማሪዎች በደንብ እንዲመለከቱ ያድርጉና በስዕሎቹ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡-** (ስነ ጽሁፍ) በሚለው ክፍል ስለ አፈታሪክ አጠር ያለ ማብራሪያ ያድርጉላቸውና የቀረበውን ምንባብ እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በአካባቢያቸው የሚነገሩ አፈታሪኮች ካሉ አምጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

**መረጃ መሳሪያ**

ሞዴል ዐረፍተ ነገሮች

ለማስተማሪያ የተዘጋጁ ስዕሎች

ለማስተማሪያ የሚሆኑ አፈታሪኮች

**ግምገማ**

-ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡

-ስእሉን ተመልክተው መልዕከቱን በትክክል መረዳታቸውን መገምገም፡፡

-የአቻ ንግግር ሲያደርጉ መከታተል፡፡

-ምንባቡን በትክክል ማንበባቸውን መከታተል፡፡

-መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አንብበው እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መገምገም፡፡

-አያያዥን በመጠቀም ሀረግን ከሀረግ አረፍተ ነገርን ከአረፍተነገር ጋር ማያያዛቸውን መከታተል

-ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽን ተጠቅመው አረፍተ ነገር መመስረታቸውን ማረጋገጥ፡፡

-የስነ ፅሁፍ ንባብን መስጠትና የእውቀት እድገታቸውን ማረጋገጥ፡፡

**3.በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ ተግባር አንድ**

| | |
|---|---|
| ሀ/እንቁጣጣሽ | የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ |
| ለ/እሬቻ | የኦሮሞ ባህላዊ በአል |
| ሐ/ደራሮ | የጌዴኦ ዘመን መለወጫ |
| መ/ጊፋታ | የወላይታ ዘመን መለወጫ |
| ሠ/ፍቼ | የሲዳማ ዘመን መለወጫ |

ረ/ዮ መሳላ የከምባታ ዘመን መለወጫ

ሰ/ያ ሆዴ ማስቃላ የሀዲያ ዘመን መለወጫ

ሸ/ጋዜ ማስቃላ የጎፋ ዘመን መለወጫ

ቀ/ ያኦ ማስቃላ የኦይዳ ዘመን መለወጫ

በ/ዮ ዮ ማስቃላ የጋሞ ዘመን መለወጫ

**ተግባር 2**

1.ዘዴ

2.ያልተከናወነ

3.አጽንኦት

4.አያሌ

5.ያልጠነከረ

**ተግባር 3 ከላይ የቀረበውን መልመጃ (ተግባር) ሰርታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረበውን ባዶ ቦታ በተስማሚ ቃል አሟሉ፡፡**

ሀ. ቆንጆ ሐ. ይወደዳል

ለ. መጥፎ መ. ጠባብ

**ክፍለትምህርትአራት**

**ተግባር 2** 1. መ 2. መ 3. ለ 4. ሐ 5. መ

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

**ተግባር 1 ከዚህ በታች የቀረቡትን መመሪያዎችና ትዕዛዞች አንብባችሁ በቡድን በመሆን ትዕዛዝ የሆነውን በትዕዛዝ ቦታ መመሪያ የሆነውን በመመሪያ ቦታ ጻፉ፡፡**

1. መመሪያ 3. ትዕዛዝ 5. ትዕዛዝ

2. መመሪያ 4. ትዕዛዝ 6. መመሪያ

**ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**ተግባር 1 ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አጣምሯቸው፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.እና | 4.ወይስ | 7. ወይም | 10. ወይም |
| 2.ምክንያቱም | 5.ነገርግን | 8. ምክንያቱም | |
| 3.ና | 6.ና | 9. ነገርግን | |

**ተግባር 2 ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ወደ አንድ ዓረፍተ ነገር ቀይሩ፡፡**

1.አበበ ቁርሱን በላና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

2.ሁለቱም ልጆች አይነጋገሩም ምክንያቱም ትላንት ተጣልተዋል፡፡

3.ከገበያ ልግዛልህ ?ወይም ከሱቅ ልግዛልህ?

4.ትምህርት ቤት መጥተህል  ሆኖም እኔና አንተ  አልተገናኘንም፡፡

## ምዕራፍ ሦስት (9 ክፍለጊዜ)

### አውደ ርዕስ- የሴቶች ሚና

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የክርክሮችንና የውይይቶችን ሀሳብ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፡፡
- ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ውስብስብ (ጠንካራ)ቃላትን በትክክል ያነባሉ፡፧
- የእለት ተእለት እንቅስቃሴ መረጃቸውን ይጽፋሉ
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ ፡፡
- ነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡
- በአያያዥ ቃላት ድርብ ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ቀለል ያሉ ስነ ጽሁፋዊ ምንባቦችን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

**ማዳመጥ**

- ስለ ክርክሩ ሂደት በደንብ አዳምጠው ክርክር ያቀርባሉ፡፡
- ጭውውቱን በማዳመጥ ጭውውት ያቀርባሉ፡፡

**ማንባብ**

- ምንባቡን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

- የቃላትን ዓውዳዊ ፍች ይናገራሉ፡፡

**መናገር**

- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ተመስርተው ይናገራሉ፡፡
- የቃላትን ዓውዳዊ ፍች ይናገራሉ፡፡
- ስለራሳቸው ታሪክ ይናገራሉ፡፡

**መፃፍ**

- እለታዊ ማስታወሻ ምን እንደሆነይናገራሉ፡፡
- እለታዊ ማስታወሻ ይጽፋሉ፡፡

**ቃላት**

- ተመሣሣይ ቃለትን ያዛምዳሉ ፡፡
- ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ፡፡

**ሰዋሰው**

- ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አውቀው ይመሰርታሉ፡፡
- ዓረፍተ ነገሮችን በስልታቸው ይከፍላሉ፡፡
- ነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

**ሥነ-ጽሑፍ**

-የቀረበላቸውን ምንባብ አንብበው ይረዳሉ፡፡

-የሚቀርብላቸውን ተረት መልእክት ይናገራሉ፡፡

-አጫጭር ግጥሞችን ያነባሉ፡፡

- አያያዥ ቃላትን በዐረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፤

## የክፍለ ትምህርቱ ዝርዝር ይዘት

**ማዳመጥ**

- ክርክር
- ጭውውት

**ማንበብ**

- ምንባብ
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች

የቃላት ዐውዳዊ ፍች

**መናገር**

- መናገር
- የቃላት ዓውዳዊ ፍች
- የራስን ታሪክ መናገር(ግለታሪክ)

**መጻፍ**

እለታዊ ማስታወሻ

የእለታዊ ማስታዎሻ አያያዝ

**ቃላት**

- ተመሳሳይ ቃላት

- ተቃራኒ ቃላት

**ስዋስው**

ነጠላ ዐረፍተነገር

ድርብ ዐረፍተነገር

**ስነ- ጽሁፍ**

- የተረት ምንባብ

- አያያዥ ቃላት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ ፡- ማዳመጥ**

መምህር ተማሪዎቹን አስቀድመው በቡድን ያደራጇቸውና በርዕሱ መሰረት ለክርክር እንዲዘጋጁ ይንገሯቸው፡፡ ሌሎች ቡድኖችን ደግሞ ጭውውት እንዲያቀርቡ ያደራጇቸው ከዚያም ክርክር ማሟላት ያለበትን ነገር ሁሉ ያስተካክሉ ፤በመቀጠል ክርክሩን ሲያቀርቡና ጭውውቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎች በትኩረት እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም አስተያየት እንዲሰጡ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት** ተማሪዎቹ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ስዕሎች በደንብ ተመልክተው፡፡እያነፃፀሩና እያወዳደሩ እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ስዕሉን በቡድን እንዲመለከቱት ያድርጉና ለዚህ የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተረዱትን ነገር ያረጋግጡ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት** ንባብን የሚለማመዱበት ቦታ ስለሆነ አስቀድመው ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸውና የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡ በመቀጠልም ምንባቡን እራሳቸው ተማሪዎች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምን ያህል እንደተረዱ ያረጋግጡ፡፡

## የትነበርሽ

የትነበርሽ የተወለደችው በ1975 ዓ.ም በአማራ ሳይንት አከባቢ ሲሆን በተወለደች በአምስት ዓመቷ የዓይን ብርሃኗን አጣች፡፡ እናቷ ለአይን ህክምና ወደ አዲስ አበባ ቢያመጧትም ምንም ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡ ሆኖም ስድስት ዓመት ሲሞላት እናቷ ወደ ሻሸመኔ የዓይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት ላኳት፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷንም የተማረችው በዚሁ ትምህርት ቤት ነበር ፡፡ ስድስተኛ ክፍልን እንደጨረሰች በራስ መተማመኗን እንደያዘች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመማር ወደ አዲስ አበባ ሄደች፡፡

የትነበርሽ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ 12ኛ ክፍል ማየት ከሚችሉ ተማሪዎች ጋር ተምራለች፡፡ በዚያ ጊዜ ውስጥ የክበባት መሪ በመሆንና የተማሪዎች መማክርት ፕረዘዳንት በመሆንም ሠርታለች፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትጨርስ ዲግሪ ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባች ፡፡ ለሰዎች መብት መከበር በነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ የህግ ትምህርት ለማጥናት ወሰነች፡፡ የህግ ትምህርቷን በማጥናት ሰዎች እኩል መብቶች እንዳሏቸው ተረዳች፡፡ በዚህም የአካል ጉዳተኛና የችግረኛ ሰዎችን መብቶች ለማስከበር ወሰነች፡፡ በዚሁ መሠረት በ1998 ዓ.ም በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪዋን እንደጨረሰች የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኝነትና ልማት ማዕከል በማቋቋም

ሂደት በንቃት ተሳተፈች፡፡ ምኞቷን እውን ለማድረግ ጥረቷን ቀጠለች፡፡ በማዕከሉም ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ሆና እየሠራች ነው፡፡ ልበ ብርሃኗ የትነበርሽ ባበረከተችው ከፍተኛ አስተዋፅኦ በሀገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሽልማቶችን አግኝታለች ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ አገልግሎት የትምህርት መስክ ሁለተኛ ድግሪዋን ይዛለች ፡፡ ባለትዳርና የሁለት ሴት ልጆች እናት የሆነችው ይቺ ወጣት አሁንም የተዘነጉ ወገኖች መብት እንዲከበር በመታገል ላይ ትገኛለች ፡፡ አካል ጉዳተኞች ጠንካሮችና ራዕያቸውን ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን እያሳየች ነው ፡፡

(ሲዳ ፡፡ 2010 ኢዱኬሽን ጀንደር ኢኳሊቲ ገጽ 1-7 ተሻሽሎ የተወሰደ)

**ተግባር1. ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ ፡፡**

ሀ. የትነበርሽ የዓይን ብርሃኗን ያጣችው ገና ስትወለድ ነበር ፡፡

ለ. ወደ ዓይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት የመጣችው ስድስት ዓመት ሲሞላት ነበር፡፡

ሐ. እሷ ባበረከተችው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምክንያት በርካታ ሽልማቶችን ማግኘት ችላለች፡፡

መ. የትነበርሽ ለአካል ጉዳተኞችና ለተዘነጉ ወገኖች ምሳሌ ልትሆን ትችላለች፡፡

**ተግባር2.. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን አማራጭ በመምረጥ መልሱ ፡፡**

1.የትነበርሽ የህግ ትምህርቷን ለመማር የወሰነችው ለምን ነበር ?

ሀ. ለሰዎች መብት መከበር ከነበራት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ፣

ለ. በጓደኞቿና በቤተሰቦቿ ከፍተኛ ጫና ስለነበረባት፣

ሐ. ከልጅነቷ ጀምሮ በሚደርስባት ተጽዕኖ ምክንያት፣

መ. ሁሉም መልስ ይሆናል፡፡

2.የትነበርሽ በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያገኘችው መች ነበር?

ሀ. በ1998 ሐ. 1999

ለ. በ2004 መ. 2006

3.የትነበርሽ ሁለተኛ ዲግሪዋን የያዘችው በየትኛው መስክ ነበር ?

ሀ. በአከባቢ ሳይንስ ሐ. በአከባቢ ጥበቃ

ለ. በማህበራዊ አገልግሎት        መ. መልሱ አልተሰጠም

4.የአካል ጉዳተኝነትና ልማት ማዕከልን በማቋቋሟ ምክንያት

ሀ. ምኞቷን እውን አድርጋለች ።

ለ. ጥረቷን አሳክታለች ።

ሐ. የሌሎችን መብት ማስከበር ችላለች ።

መ. ሁሉም መልስ ነው።

ክፍለ ትምህርት አራት ሲያስተምሩ ቀጥተኛ ፍችና ዓውዳዊ ፍች ያላቸውን ልዩነት ቀድመው ይግለፁላቸው። በመቀጠልም ምሳሌ በመስጠት ያነቃቋቸው ። ከዚያም የቀረበውን የክፍል ስራ እንዲሰሩ ያድርጓቸውና በመጨረሻም ከተማሪዎች ጋር አብራችሁ ስሩ። በማያያዝም ተማሪዎች የራሳቸውን ታሪክ እንዲናገሩ ያድርጉ።

ክፍለ ትምህርት አምስት -መምህር በመጀመሪያ እለታዊ ማስታወሻ ምን እንደሆነ በደንብ ያስረዷቸው፣ ቢቻል ሞዴል የሆነ ዕለታዊ ማስታወሻ ያንብቡላቸው፤ ከዚህ በመነሳት ለእለታዊ ማስታወሻ የቀረበውን ምንባብ በቡድን እንዲያነቡና እንዲወያዩበት ያድርጉ ።በምሳሌው  መሰረት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ በመጨረሻም የእለት ማስታወሻቸውን ጽፈው እንዲያመጡ ያድርጉ በማንኛውም ስራቸው ያበረታቷቸው።

ቀን04/01/2014

ዛሬ ከቤት የወጣሁት በጧት ነው ። ቤተሰቦቼም ከመኝታቸው ገና ስላልተነሱ ቁርሴን የመብላት አጋጣሚ አላገኘሁም። ቀጥታ ደብተሬን ይዤ ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ ። አንድ ክፍል ውስጥ ገብቼ  የቤት ስራዬን መስራት ጀመርኩኝ ። የቤት ስራዬን ሰርቼ ስጨርስ ተደወለና ተማሪዎች ገቡ። እኔም ወደ ክፍሌ

በመግባት ትምህርቴን ቀጠልኩ ። ልክ 6፡15 ሲሆን ተደወለና ወደ ቤቴ ሄድኩኝና ምሳዬን በላሁ። ከብቶችን እንድጠብቅ ተነገረኝና እስከ 12 ሰዓት ስጠብቅ ቆይቼ ወደቤት ተመለስኩ ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ያጋጠመኝ ክፉ ነገር አልነበረም።

**ክፍለ ትምህርት ስድስት** የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የቃላትን ተመሳሰይና ተቃራኒ ፍች ያሰሯቸው ።

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡-** በተማሪው መጽሐፍ ላይ ካለው ማስታወሻ በመነሳት ስለ ነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገር ያብራሩላቸው። ከዚያም ገለፃ ያድርጉላቸውና የተወሰኑ ነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን በማቅርብ በምሳሌው መሰረት ነጠላ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው፡፤ በሁለተኛው ስራቸው ሁለት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አያይዘው ድርብ ዓረፍተ ነገር ሰርተው ያሳዩአቸው። በመጨረሻም የተሰጠውን ስራ እንዲሰሩ ይዘዟቸውና እየተዘዋወሩ ይደግፏቸው።

**ክፍለ ትምህርት ስምንት** አስቀድመው ስለ ተረት ምንነት በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፤ ከዚያም ተረቱን እንዲያነቡ ያድርጓቸው።ቢችሉ መምህር ከምንባቡ በፊት አንድ ተረት በቃል ቢነግሯቸው መልካም ነው ።በመቀጠልም ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው።

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ** አያያዥ ቃላትን የሚመለከት ነው። አያያዥ ቃላት ምን እንደሆኑ፣እንዴት ቃላትን ሀረጋትን ፣ዓረፍተ ነገሮችን እንደሚያይዙ በደንብ ያስተምሯቸው።ከዚያም በተለማመዱት መሰረት የተሰጠውን የክፍል ሥራ እንዲሰሩ ያድርጓቸው። በመጨረሻም የተሰጣቸውን የቤት ሥራ እንዲሰሩ ይዘዟቸው።

## መርጃ መሳሪያ

በቻርት ላይ የተጻፉ አያያዥ ቃላት

ተረቶች

የነጠላና ድርብ ዐረፍተ ነገር ቻርት

**መገምገሚያ**

-የተግባር ምዘና (ለቃላት ዐውዳዊ ፍች መስጠታቸውን ማረጋገጥ)

-የቃል ጥያቄ

-ምልከታ

-አያያዥ ቃላትን በአግባቡ መጠቀማቸውን በጽሁፍ ፈተና ማረጋገጥ

-ነጠላ ዐረፍተነገር እንዲመሰርቱ በማድረግ

-እለታዊ ማስታዎሻቸውን እንዲጽፉ በማድረግ

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት አራት**

**ተግባር 1 በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ሥራ/ደሞዝ
2. ደነገጠ
3. የሚጠጣ የተፈጥሮ ውሃ
4. ከሸክላ የተሰራ ውሃ መቅጃ
5. ስራ መስራት
6. ጥሩ አመለካከት
7. ተናደደ

8. አስተካከለ/አቃና

9. ተስተካከለ

10. ምግብ

**ክፍለትምህርት አምስት**

**ተግባር 4 ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት በምዕላድ ከፋፍላችሁ አስቀምጡ፡፡**

1- ኢትዮጵያ-አዊ-ነት

2-ትክክል-ኛ-ነት

3- ብልጽግና-ችን

4-አካሄድ-ኣቸው

5-ጠባብ-ነት

6- ሰብእ-ኣዊ -ነት

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ**

**ተግባር 2 ከላይ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት በመምረጥ ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች አጣምሩ፡፡**

1. ስለዚህ/ይሁን እንጂ
2. እንጂ
3. ቢሆንም
4. ቢሆንም
5. ይሁን እንጂ

**ምዕራፍ አራት** (9) ክፍለጊዜ

# አካባቢያችን

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-

- የጭውውቱን ሀሳብ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፡፡
- ስለ አንድ አካባቢ አጠቃላይ ሁኔታ በዝርዝር ይናገራሉ፡፡
- ገረፍ ገረፍ የንባብ ስልትን ተጠቅመው መረጃ ይሰበስባሉ፡፡
- ለምን፣ እንዴት የሚሉትን ቃላት በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን ፍች አውቀው ይጠቀማሉ፡፡
- ጾታን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡
- ምሳሌያዊ ንግግሮችን አምጥተው ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ፡፡
- ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን ነጥለው ያወጣሉ፡፡
- ሥርአተ ነጥቦችን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማ

## ክፍለትምህርት አንድ

- የጭውውቱን ሀሳብ አዳምጠው የተረዱትን ይናገራሉ፡፡
- ስላዳመጡት ነገር ገለጻ ያደርጋሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ሁለት**

- ስላነበቡት ነገር መልሰው ይናገራሉ፡፡
- ስለአካባቢ ጥበቃ የተረዱትን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ሦስት**

-ምንባቡን በትክክል ያነባሉ፡፡

-ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡

**ክፍለትምህርት አራት**

- መጠይቃዊ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡
- መጠይቃዊ ቃላትን በጽሁፋቸውና በንግግራቸው ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

- የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን ለይተው ያወጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡-**

- ስለፆታ ምንነት ይናገራሉ፡፡
- አንስታይና ተባዕታይ ፆታን በትክክል በቃልም በጽሑፍም ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት ፡-**

- ምሳሌያዊ ንግግሮችን ተጠቅመው ይናገራሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ስምንት፡-**

- ቅጥያዎችን ለይተው ያወጣሉ
- ቅጥያዎችን ያጣምራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡-**

- ድርብ ሰረዝን በጽሑፍ ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፡
- የሦስት ነጥብ አገልግሎትን ይናገራሉ፡፡

**ዝርዝር ይዘት**

**ክፍለትምህርት  አንድ**

- ጭውውት
- አዳምጦ መናገር

**ክፍለ ትምህርት ሁለት**

- መናገር
- የአካባቢ ጥበቃ

**ክፍትምህርት ሦስት**

- ምንባብ
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች

**ክፍለትምህርት አራት፡-**

- መጠይቃዊ ቃላትና
- አገልግሎታቸው

**ክፍለትምህርት አምስት**

- የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት

**ክፍለትምህርት ስድስት**

- ፆታ
- አንስታይና ተባዕታይ ፆታ

**ክፍለትምህርት ሰባት**

- ምሳሌያዊ ንግግር

**ክፍለትምህርት ስምንት**

- ቅጥያዎች
- ቅጥያዎችን መነጠልና ማጣመር

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ ፡-**

- ድርብ ሰረዝ
- ሦስት ነጥብ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ (ማዳመጥ)** ይህ ክፍል ጭውውትን የሚመለከት ነው፡፡ መምህር ፣መጀመሪያ ጭውውቱን ከማንበብዎ በፊት ስለ ጭውውት ምንነት ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል እባኮትን መምህር ጭውወቱን ያስደምጧቸው፡፡ጭውውቱን ካስደመጡ በኃላ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

**ጭውውት**

ላዌ - ስማ ስማ እባክህ ! ጥቅም አይደልለኝም ነው ያልከኝ? ድንቄም ስጋ ለባሽ መሆንህን ዘነጋህው እንዴ?

ሰንበቶ - ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?

ደያሶ - አልገባኝም ምንድነው ? የሚያጨቃጭቃችሁ?

ላዌ - ጭቅጭቅ አይደለም ፣ማለት የፈለኩትንማ እሱ ራሱ ያውቀዋል፡፡

**ሰንበቶ** - ምንድነው የማውቀው ? እስኪ ግልጽ አድርጊልኝ?

**ደያሶ** - ልክ ብለሀል ነገሮችን ግልጽ አድርጎ መናገር ጥሩ ነው፡፤

**ላዌ** - ለዚህ ምን ግልጽነት ያስፈልጋል ፣የጥቅም ሰው መሆንህን ሀገር ሁሉ ያውቀዋል፡፡

**ሰንበቶ** - ስሚ እኔ የጥቅም ሰው አደለሁም፡፡ የሌሎችን ጥቅም ለማስቀደም የምጥር ሰው ነኝ

**ደያሶ** - አንቺ! ከምን ተነስተሽ ነው እንዲህ ለማለት የቻልሽው ?

**ላዌ** - በቅርበት ስለማውቀው ነዋ !

**ሰንበቶ** - የምታውቂኝ ቢሆንማ እንዲህ አትይኝም ነበር፡፡

**ደያሶ** - እርግጠኛ ነሽ ?

**ላዌ** - እርግጠኛማ ነኝ ! እርግጠኛ ባልሆንማ ለምን እጨቃጨቃለሁ ?

**ሰንበቶ** - ተይ ተይ ይህ ሁሉ ንትርክ ባለፈው ጊዜ በሰው ወሬ ስለተጋጨን ነው፡፡

**ደያሶ** - እንደዛማ ከሆነ አንቺም የሰውን ወሬ ሰምተሽ ስለአንድ ሰው መናገር አትችይም፡፡

**ላዌ** - አይ ! የሰው ወሬ የሚባል ነገር የለም፤ ከማየው ነገር ተነስቼ ነው፡፡

**ሰንበቶ** - እሽ ! ካልሽ ጥሩ እኔ ግን አንቺ እንደምትይኝ አይነት ሰው አደለሁም፡፡

**ደያሶ** - በቃ ሁለታችሁም ጭቅጭቃችሁን ትታችሁ እንደድሮአችሁ ሁኑ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት፡-** ( መናገር )ይህ ክፍል የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከት ነው፡፡ መምህር ወደ ትምህርትዎ ከመግባትዎ በፊት በመጀመሪያ ስለአከባቢ ጥበቃ ማብራሪያ ይስጡ፡፡ በመቀጠልም የአካባቢ ጥበቃ በሚል የቀረበውን ምንባብ ያንብቡ፡፡ በመቀጠልም ከምንባቡ ያገኙትን መልዕክት እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም የደን ጭፍጨፋ የሚያስከትለውን ጉዳት በቡድን በመሆን መረጃ ሰብስበው በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት፡-** (ምንባብ) ይህ ክፍል ምንባብን የሚመለከት ነው፡፡ መምህር ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በትክክል እያነበቡ መሆናቸውን ይከታተሉ፡፡ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት** (መፃፍ) መምህር በመጀመሪያ ለተማሪዎቹ ስለመጠይቃዊ ቃላት ምንነት ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም መጠይቃዊ ቃላትን በአረፍተነገር ወስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ምሳሌ በመስጠት

ያሳዩአቸው፡፡ በመቀጠልም መጠይቃዊ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ተጠቅመው መፃፋቸውን ያረጋግጡ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት ፡-(ቃላት)** ስለሚጠብቁና ስለሚላሉ ቃላት አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ ቃላት ጠብቀው ወይም ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን የፍች ለውጥ በምሳሌ እያስረዱ ያሳዩአቸው፡፡ በመቀጠልም በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት የተሰጣቸውን ቃላት በትክክል መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍል ትምህርት ስድስት ፡-** ስዋስው በሚለው ከፍል ፆታን የሚመለከት ትምህርት ቀርቧል፡፡ ስለ አንስታይና ተባዕታይ ፆታ አጠር ያለ ገለፃ ያድረጉላቸውና መልመጃዎቹን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም አንስታይና ተባዕታይ ፆታን በትክክል ለይተው ማስቀመጣቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡-** ሥነ- ጽሑፍ በሚለው ክፍል ስለምሳሌያዊ ንግግር ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያ ስለምሳሌያዊ ንግግር አጠር ያለ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠልም ምሳሌ በመስጠት በውስጣቸው የሚያስተላልፉትን መልዕክት ይንገሯቸው፡፡ በመጨረሻም በአካባቢያቸው የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አምጥተው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት፡-** በመጀመሪያ ስለ ቅጥያ ምንነት ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም ቅጥያዎች በቃል ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ ይንገሩ፡፡በመቀጠልም ቅጥያዎችን ከቃል ውስጥ እንዴት መነጠል እንዳለባቸው በምሳሌ በማስደገፍ ያሳዩአቸው፡፡ከዚያም ቅድመና ድህረ ቅጥያ ያለቸውን ቃላት በመስጠት ዋናውን ቃል ለይተው እዲያስቀምጡ ይንገሯቸው፡፡በመጨረሻም በትክክል ለይተው ማስቀመጣቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡-** በመጀመሪያ ስለ ስርዓተ ነጥብ ምንነት ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡በመቀጠልም ስለድርብ ሰረዝና ስለሶስት ነጥብ ምንነትና አገልግሎት ይንገሯቸው፡፡ከዚያም እንዴት በዓረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም እንዳለባቸው ምሳሌ

በመስጠት ያሳዩአቸው፡፡ በመቀጠልም የተሰጣቸውን መልመጃ በትክክል መስራታቸውን ይከታተሏቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ**

- በቻርት ላይ የተሰሩ ሥርዐተ ነጥቦች
- ነጠላ ዐረፍተነገሮች
- በቻርት ላይ የተሰሩ መጠይቃዊ ቃላት
- ሞዴል ምሳሌያዊ ንግግሮች

**መገምገሚያ**

- ተግባራዊ ምዘና
- የግል ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ፈተና
- የተግባር ሥራ
- ምልከታ

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለትምህርትአምስት**

**ተግባር 1 ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍች ለይታችሁ**

**ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡- ጠላት፤** ሲጠብቅ አለመውደድን ፡፡

ሲላላ ባለጋራን ያመለክታል፡፡

| ቃል | ሲጠብቅ | ሲላላ |
|---|---|---|
| 1. ድል | ሞቅ ያለ | ማሸነፍ |
| 2. አዛባ | አናጋ | እበት |
| 3. አያት | ተመልከታት | የእናትና የአባት ወላጅ |
| 4. ሽፍታ | በሰውነት ላይ ሽፍብሎ የሚወጣ | አመፀኛ |

**ተግባር 2**

| | | |
|---|---|---|
| 5. ከፍታ | ከፍ ያለ ቦታ | የተከደነውን መግለጥ |
| 6. ጥሬ | ለፍቼ | ያልበሰለ |
| 7. ፍራሽ | ፍርስራሽ | ለመኝታ የሚሆን |
| 8. ሰፊ | ትልቅ | ልብስ የሚሰፋ |
| 9. ረጋ | በአንድ ቦታ ሆነ | ችኮላውን ተው |
| 10.ለጋ | መታ | ወጣት/ እንቡጥ) |

ክፍለ ትምህርት ስድስት

**ተግባር 1**

| | |
|---|---|
| 1.ልጅ | ወንድ/ተባዕታይ |
| 2.አለሚቱ | ሴት/አንስታይ |
| 3.ልጅቷ | ሴት |
| 4.አለሙ | ወንድ |
| 5.ድንጋይ | ወንድ |

**ተግባር 3**

1ደከመች　　　　አለው

2.ደከመው　　　　አለው

3.አንበሳ　　　　የለውም

4.ወይፈን　　　　የለውም

5.ጊደር　　　　የለውም

6.ጎረምሳ　　　　የለውም

7.ልጃገረድ　　　　የለውም

**ክፍለ ትምህርት ስምንት**

**ተግባር> 2**

| ***ቃል*** | ***ዋና ቃል*** | ***ቅጥያ*** |
|---|---|---|
| 1.መጣችሁ | መጣ | -ኣችሁ |
| 2.ተራራማ | ተራራ | -ኣማ |
| 3.ደጋማ | ደጋ | -ኣማ |
| 4.ብልጠት | ብልጥ | -ኧት |
| 5.ማህበራት | ማህበር | -ኣት |

ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

ተግባር 1 ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ በመመልከት በምሳሌው መሰረት ቀጣዮቹን ጥያቄዎችን መልሱ።

ሀ/ ድርብ ሰረዝ      ድርብ ሰረዝ

ለ/ ሶስት ነጥብ

ሐ/ ድርብ ሰረዝ      ድርብ ሰረዝ    ድርብ ሰረዝ

መ/ ሶስት ነጥብ

**ምዕራፍ አምስት (9ክፍለጊዜ)**

## የግለሰብ የህይወት ታሪክ

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች**

- የሌሎች ተማሪዎችን ልምድ በማዳመጥ የራሳቸውን ልምድ ይናገራሉ፡፡
- ስዕሎች፣ ካርታዎችና ሰንጠረዥች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ይናገራሉ፡፡
- ጥልቅ የንባብ ስልትን በመጠቀም የንባቡን መልዕክት ያወጣሉ፡፡
- ዋናና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የአረፍተ ነገር ስልቶችን ተጠቅመው ይጽፋሉ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ይጠቀማሉ፡፡

**ዝርዝር ዓለማ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ**

- የሚነገራችውን ልምድ አዳምጠው አስተያየት ይሰጣሉ፡፡
- የራሳቸውን ልምድ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያካፍላሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት**

- ስለተመለከቱት ስዕልና ግራፍ ይናገራሉ፡፡
- ሰንጠረዦቹ የያዙትን መልዕክት ያስረዳሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት ፡-**

- የሚቀርብላቸውን ስዕል ተመልክተው ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

- ስዕሎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ያብራራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት ፡-**

- የቀረበላቸውን ንባብ አንብበው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይሰራሉ፡፡
- ከምንባቡ ስለግለሰቧ የሰሙትን ታሪክ አሳጥረው ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

- ዋና ሀሳብ የያዘውን ዓረፍተ ነገር ይለያሉ፡፡
- ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
- አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት**

- ጥልቅ ንባብን አውቀው ይጠቀማሉ፡፡
- የቀረበውን ምንባብ አንብበው መረጃ ያቀርባሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ሰባት**

- የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው ያሳያሉ፡፡
- የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን አውቀው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ስምንት**

- ፈሊጣዊ ንግግርን ከንባብ ውስጥ ያወጣሉ ፡፡
- ፈሊጣዊ ንግግርን በንግግራቸውና በጽሁፋቸው ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ**

- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ይሰጣሉ፡፡

**ዝርዝር ይዘት**

**ክፍለትምህርት አንድ**

***ማደመጥ***

ልምድ ማካፈል

**ክፍለትምህርት ሁለት**

- መናገር
- ስዕሎችን ካርታቸውንና ሰንጠረዦችን ተመልክቶ መናገር

**ክፍለ ትምህርት ሦስት**

- በስዕል ላይ ተመስርቶ ገለፃ ማድረግ

**ክፍለትምህርት አራት**

- - ንባብ
- የግለሰብ ህይወት ታሪክ

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

- ዋና ዓርፍተ ነገር
- ዝርዝር ዓረፍተ ነገር
- አንቀጽ

**ክፍለትምህርት ስድስት**

- የንባብ ስልቶች
- ንባብ

**ክፍለ ትምህርት ሰባት**

- ባለቤት
- ተሳቢ
- ገላጭ
- ማሰሪያ አንቀጽ

**ክፍለትምህርት ስምንት**

- ፈሊጣዊ ንግግር

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ**

- የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ

- ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች

## የትምህርቱ አቀራረብ

ክፍለ ትምህርት አንድ (ማዳመጥ) መምህር ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይጀምሩ፡፡ መምህር እባኮትን ከዚህ በመቀጠል ምንባቡን ያንብቡላቸው፡፡በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በቃል እንዲመልሱ ያደርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች የራሳቸውን ልምድ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው፡፡

### የሳሪክ ልምድ

ሳሪክ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ልምዱን ሲያካፍልም እንዲህ ይላል፡፡ ስድስተኛ ክፍል የምማረው እራሴን እየረዳሁ ነው፡፡ አስፈላጊ ወጪዎችን የምሸፍነውም በራሴ ነው፡፡ሌላ እኔን መርዳት የሚችል ሰው የለኝም፡፡ ስለዚህ ባለሁበት ትንሽ ከተማ ሊስትሮ በትርፍ ጊዜዬ እሰራለሁ፡፡ የትምህርት ሰአቴን እንዳይነካብኝ በጣም ተጠንቅቄ ነው የምሰራው፤ በቀን ውስጥ አንዳንዴ አምስት ጫማ አንዳንዴ ደግሞ እስከ አስር ጫማ እጠርጋለሁ፡፡በዚህም በቀን ከ20–50 ብር አገኛለሁ፡፡ በቀን በባንክ አካውንቴ 10 ብር አስቀምጣለሁ፡፡ በተጨማሪም እሁድ እለት ቤት ለቤት በመሄድ የቤተሰብ ጫማ አፀዳለሁ፡፡በዚህም ጥሩ ገቢ አገኛለሁ፡፡ በአሁን ሰዓት ጥሩ ሁኔታ ላይ እገኛለሁ፡፡ በባንክ አካውንቴ ስምንት ሺህ ብር አለኝ ፡፡ወደፊት የበለጠ ጠንክሬ ከዚህ የተለየ ስራ ለመስራት ሀሳብ አለኝ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት ፡-** ይህ ክፍል መናገርን የሚመለከት ነው መምህር በቅድሚያ ለተማሪዎችዎ ከሥዕል፣ ከካርታዎችና ከሰንጠረዦች መልእክትን እንዴት መረዳት እንደሚችሉ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠልም በሰንጠረዥና በግራፍ የቀረበውን በማሳየት ከሰንጠረዦችና ከግራፉ ላይ የተረዱትን መልእክት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የክፍላቸውን ተማሪዎች ፆታና እድሜ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ሰርተው በማምጣት እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለትምህርት ሦስት**

ከስዕል ላይ መልዕክት እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም ስዕሉን በመመልከት የያዘውን መልዕክት እንዲገልፁ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት** (ማንበብ) ይህ ክፍል ማንበብን ይመለከታል፡፡ምንባቡን ከማስነበቦ በፊት ከምንባቡ የወጡ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ከምንባቡ በኋላ ከምንባቡ ውስጥ ያገኙትን ፍሬ ነገሮች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ስለግለሰቦች የህይወት ታሪክ ከዚህ በፊት የሰሙት ካለ ጽፈው በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡

**ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ**

ዶክተር ቦጋለች ገብሬ የተወለደችው ከአዲስ አበባ 355 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደቡብ ክልል ውስጥ በምትገኘው የከንባታ ጠንባሮ ዞን ባቾ በተባለች ትንሽ መንደር ነው፡፡ ዶ/ር ቦጋለች በተወለደችበት ዘመን በባቾ አካባቢ የትኛዋም ሴት ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ አይፈቀድላትም ነበር፡፡ ሴት ልጅ ከማጀት ጉዳዮች አልፋ ለትልቅ ቁም ነገር ትደርሳለች ተብሎ

በማህበረሰቡ አይታሰብም፡፡ ይልቁንም ሴቶችን የሚጫኑ ልዩ ልዩ ጎጂ ልማዶች የሚከናወኑበትና የሴት ልጅ ግርዛት የተስፋፋበት ጊዜ ነበር፡፡

ዶክተር ቦጋለች ወደ አጎቷ ቤት በመሄድ ከተማሩ አጎቷና የአጎቷ ቤተሰቦች ፊደልን ተምራለች፡፡ ከዚያም በመቀጠል ማንበብና መፃፍም ቻለች፡፡ በመጠንከር ወላጆቿ የሚያዟትን ስራ በትጋት በመስራት ከአጠናቀቀች በኋላ በሚነደው እሳት ብርሃን ቁጭ ብላ ታጠና ነበር፡፡ ትጋቷንና ጥንካሬዋን ያዩ አባቷ ትምህርት ቤት እንድትገባ ፈቀዱላት፡፡ በቀን እስከ 6 ኪሎ ሜትር በመጓዝ ትምህርቷን ቀጠለች፡፡ በዘጠኝ አመቷ የአራተኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቀቀችና ወደ አምስተኛ ክፍል ገባች፡፡ ይህም በዚያ አካባቢ ካሉት ሴት ተማሪዎች በላይ የተማረች አደረጋት፡፡ እሷም ለመንደሩ ሰዎች ማመልከቻ በመፃፍ ትረዳቸው ነበር፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት አባት በወንድ ልጁ ስም የእከሌ አባት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን እናት ደግሞ በሴት ልጇ የእከሊት እናት ተብላ ነው የምትጠራው፡፡ የቦጋለች ጉብዝና ግን ይህን ታሪክ ቀየረውና አባትየው የቦጋለች አባት እየተባሉ መጠራት ጀመሩ፡፡

ቦጋለች የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በዚያው በመጨረስ ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በመነን ትምህርት ቤት ተምራለች፡፡ ከዚያም ነፃ የትምህርት እድል በማግኘት ወደ እስራኤል ሄዳ ተምራለች ፡፡ከዚያም በተለያዩ ሀገራት በመሄድ ተምራ በ "ኢፒዴሚሎጂ" የዶክተሬት ዲግሪ ይዛለች፡፡ ደ/ር ቦጋለች በአፀፋው "ሴት ልጅ መደቧ ማጀት ነው" የሚለውን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከንባታ ወጣት ነች፡፡

**(ምንጭ ኩሜጌ ቢሮ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ 2003 ዓ/ም)**

**ተግባር1. ከላይ የቀረበውን ምንባብ በአነብባችሁት መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ዶክተር ቦጋለች ገብሬ የተወለደችው በየትኛው አካባቢ ነው?
2. የዶክተር ቦጋለች አባት፣የቦጋለች አባት እየተባሉ መጠራት የጀመሩት ከመቼ ወዲህ ነው?

3. በመጀመሪያ ትምህርቷን የጀመረችው ቤተሰቦቿ ፈቅደውላት ነው?

**ተግባር2. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡-**

1. የቦጋለች ቤተሰቦች አቅም ስለሌላቸው ቦጋለች ትምህርቷን ያቋረጠችው አራተኛ ክፍል ነው፡፡
2. ቦጋለች ምንም ትምህርት ብትከለከልም በራሷ ብርታትና ፍላጎት ነው ፊደል ፣ማንበብና መፃፍ የለመደችው፡፡
3. ከሀገሯ ወጥታ ወደ አዲስ አበባ የሄደችው እዚያ ያሉ ቤተሰቦቿ ጋ ለመኖር ነበር ፡፡
4. ደብዳቤና ማመልከቻዎችን የምትጽፍላቸው በአካባቢው ላሉ ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ሰዎች ነበር፡፡
5. እስከ ውጪ ሀገር ለትምህርት መሄዷ የመማር ፍላጎቷን ትልቅነት ያሳያል፡፡

**ተግባር 3. ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ፡**

1. የቦጋለች አባት ቦጋለች ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ የፈቀዱላት መቼ ነበር?

   ሀ/ ማንበብና መፃፍ ከጀመረች በኋላ ለ/ እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ

   ሐ/ የቤት ስራ ስለማትሰራ መ/ ለና ሐ መልሰ ናቸው

2. ቦጋለች ወደ አምስተኛ ክፍል ስትገባ የመጀመሪያዋ ሴት ተማሪ ሆነች ሲባል

   ሀ/ ሌሎች የተማሩት ከዚያ በታች ነበር፡፡ ለ/ ሌሎች አልተማሩም ነበር ፡፡

   ሐ/ ሌሎች የተማሩት ከዚያ በላይ ነበር ፡፡ መ/ መልስ የለም

3. "አንድ ሰው ጠንክሮ ከታገለ ምንም ነገር አያሸንፈውም፡፡" የሚለው ቃል ከቦጋለች ህይወት አንፃር

ሀ/ እውነት ነው  ለ/ ትክክል አይደለም

**ክፍለ ትምህርት አምስት** (አንቀጽ መፃፍ) መምህር በመጀመርያ ስለ አንቀጽ ምንነት በአጭሩ ይግለፁ፡፡በመቀጠልም በአንቀጽ ውስጥ ዋና አረፍተ ነገርና ዝርዝር አረፍተ ነገሮች የሚኖራቸውን ሀሳብ ይግለፁ፡፡ ከዚያም አጠር ያለ አንቀጽ (ጽሁፍ) በመስጠት ዋናና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጓቸው፡፡በመቀጠልም በትክክል ለይተው መፃፋቸውንም ይከታተሏቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት** አንብቦ መረዳት ያንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሲያሰሯቸው ተማሪዎቾዎ ሀሳባቸውን ዘርዘር አድርገው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ ጥያቄዎቹንም ከመስራታቸው በፊት ስለጥልቅ ንባብ ጥቂት ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ በተሰጣቸው ማብራሪያ መሰረት ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ካደረጉ በኋላ ባነበቡት መሰረት ጥያቄዎቹን መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት** (ስዋስው) በዚህ ክፍል መምህር በመጀመሪያ ስለ ባለቤት ፣ተሳቢ፣ገላጭና ማሰሪያ አንቀጽ ምንነት ገለጻ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባር ይንገሯቸው፡፡ ገላጭ ቃላትን በማሳወቅ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት** (ስነጽሁፍ ) በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ፈሊጣዊ አነጋገር ቀርቧል፡፡ ወደትምህርቱ ከመግባትዎ በፊት ስለፈሊጣዊ አነጋገር ምንነት ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡በመቀጠልም የተለያዩ ፈልጣዊ ንግግሮችን ከነፍችያቸው በመንገር ያስተምሩ ፡፡በተማሩት መሰረትም የሚያውቁትን ፈሊጣዊ ንግግር ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ (ቃላት) ስለቃላት ቀጥተኛ ፍች፣ ስለተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት ፍች ማብራሪያ ይስጡ፡፡ ባስተማሩት መሰረት መልመጃዎችን ይስጧቸውና መስራታቸውን ይከታተሏቸው፡፡**

**መርጃ መሳሪያ**

- ሰንጠረዥ
- ግራፍ
- ስዕል
- የግለሰብ የህይወት ታሪክ

**ግምገማ**

- አጭር ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎች
- የቡድን ስራና ጥያቄዎችን መመልስ
- የቡድን ስራ
- አቻዊ ምዘና
- የጽሁፍ ፈተና
- ምልከታ
- የክፍል ስራ

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

ተግባር 1 ከሚቀጥሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የያዘውንና ዝርዝር ሃሳብ የያዙትን ዐረፍተነገሮች ለይታችሁ አውጡ፡፡

**ዋና ዐረፍተነገር-** 1.ልጆች በጨዋታ ጊዜ የሚያዜሟቸው ዜማዎች ይለያሉ፡፡

2. ለምለምና ዘላለም በጣም የሚዋደዱ እህትና ወንድም ናቸው፡፡

3.በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሃይቆች ይገኛሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ**

**ተግባር 1 ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡ ቃላት በቡድን በመሆን ቀጥተኛ ፍችያቸውን ስጡ፡፡**

**1 ወላጅ አልባ - በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸው የተለዩአቸው**

**2 መመሪያ - ትዕዛዝ**

**3.ፍቅር - መውደድ**

**4.በጎነት -ደግነት**

**5.እርምጃ - እንስቃሴ**

**ተግባር 2 ከዚህ ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ተቃራኒያቸውን ከፊት ለፊታቸው ከቀረቡት ቃላት እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. ሐ | 5. ለ |
| 2. ሀ | 6. መ |
| 3. ሰ | 7.ሠ |
| 4. ሸ | 8 ረ |

# ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት

## ምዕራፍ ስድስት (9 ክፍለጊዜ)

### ሀገር ወዳድነት

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- የሚቀርቡትን ምንባቦች አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ሀገር በቀል እውቀቶችን አምጥተው ለክፍል ጓደኞቻቸው ይናገራሉ፡፡
- ምንባቡን አንብበው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይረዳሉ፡፡
- የተማሩትን መመሪያ ተከትለው ደብዳቤ ይጽፋሉ፡፡
- ቃላትን አዳምጠው ቀጥተኛ ፍቻቸውን በቃል ይናገራሉ
- በዐረፍተ ነገር ስልቶች ይጠቀማሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ግጥም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነባሉ፡፤

### የክፍለ ትምህርቱ አላማዎች

**ማዳመጥ**

- የሚቀርብላቸውን ንባብ አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡
- አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡

**መናገር**

- ስለ ሀገር በቀል እውቀት ይናገራሉ፡፡
- ስለባህል መድሀኒት ጥቅምና ጉዳት ይናገራሉ ፡፡

**ማንበብ**

- ምንባቡን በጥልቀት ያነባሉ።
- የምንባቡን መልእክት ጨምቀው ያወጣሉ።

**መፃፍ**

-የግል ደብዳቤ እንዴት እንደሚፃፍ ጽፈው ያሳያሉ።

- የግል ደብዳቤ ይጽፋሉ ።

**ቃላት**

- የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ይናገራሉ፡፤
- ለቀረቡላቸው ቃላት ቀጥተኛ ፍች ይሰጣሉ።

**ስዋስው**

- የአረፍተ ነገር ስልቶችን በትክክል ይጠቀማሉ።
- አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ።

**ስነ ጽሁፍ**

- ቀለል ያሉ ግጥሞችን ያነባሉ
- ስንኝና ሀረግን ለይተው ያወጣሉ።

**የክፍለ ትምህርቱ ዝረዝር ይዘቶች**

**ማዳመጥ**

- ማዳመጥ

- አዳምጦ መረዳት

**መናገር**

- ሀገር በቀል እውቀት
- ባህላዊ መድሐኒት

**ማንበብ**

- ማንበብ
- አንብቦ መረዳት

**መፃፍ**

- የግል ደብዳቤ አፃፃፍ
- የግል ደብዳቤ መፃፍ

**ቃላት**

- የቃላት ቀጥተኛ ፍች

**ስዋስው**

- የአረፍተ ነገር ስልቶች
- አረፍተ ነገር መመስረት

**ሥነ-ጽሁፍ**

- ግጥም
- ስንኝና ሀረግ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ**

እባኮት መምህር የማዳመጡን ምንባብ ከማንበቦ በፊት ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀታቸውን ለመቀስቀስ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀሙ፡፡ በመቀጠል ምንባቡን ጎላ ባለ ድምጽና ረጋ ባለ ሁኔታ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ሲያነቡላቸው በየመሀሉ ሳያቋረጡ ንባቡ እስከሚያልቅ ድረስ ቀጥታ ያንብቡላቸው፡፡ከዚያም ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች በቡድን እንዲሰሩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡ በቡድን ሆነው የሰሩትን ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉና ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ከምንባቡ ጋር የሚመሳሰል ሀገር በቀል እውቀት የሆኑ ነገሮችን በቡድን ሆነው እንዲያመጡ በቡድን ያደራጇቸው፡፡

## የባህል መድሐኒት

አቶ ሀጂ የባህል መድሐኒት ሐኪም ናቸው፡፡ የሰፈሩ ሰው ሁሉ ወደ እሳቸው ጋ በመሄድ ይታከማሉ፡፡ ሀጂ መድሐኒቱን የሚያዘጋጁት ወደ ሰፊ ደንና ዱር በመሄድ ከእጸዋት ላይ ቅጠሉን፣ፍሬውን ስሩን ወይም ቅርፊቱን ወይም ሌላውን አካል በመልቀም ያጠራቅማሉ፡፡ ከዚያም ወደ ቤታቸው በማምጣት ያደርቁታል፡፡ ከደረቀ በኂላ ይወቅጡታል፡፡በራሱ መድሐኒት የሚሆነውን ብቻውን ፣ከሌሎች ጋር ተቀላቅሎ የሚቀመመውን ቀላቅለው ይቀምሙታል፡፡ ከዚያም ለሚጠጣ፣ ለሚዋጥ፣ለሚቀባ ፣ወዘተ የሚሆነውን ይለዩና ያዘጋጁታል፡፡ ከዚያም ወደ

እሳቸው ለሚመጣው ታካሚ ከበሽታው አንፃር እሳቸው በገመቱት መጠን ይሰጡታል፡፡የመደሐኒቱ መጠን ውሳኔ በእሳቸው ነው፡፡ በእጃቸው ለክተው በሲኒ ሰፍረው ወዘተ ይሰጣሉ፡፡ መድሐኒቱ ሰውዬው ላይ ከከበደ በሽታውን እየመረመረው ፣እየተዋጋው ነው ይላሉ፡፡በመጨረሻ መደሐኒቱ በሰውነት ስለሚቆይ ማርከሻ ያስፈልገዋል በማለት የተለያዩ መጠጦችን ወይም የተለያዩ ምግቦችን በባዶ ሆድ እንዲጠጣ ወይም እንዲበላ ያዛሉ፡፡ሌላው መደሀኒቱ የሚጠላው ምግብ ብለውም የሚከለክሉት አለ፡፡ በዚህ አይነት አቶ ሀጂ ህክምናቻውን ያጠናቅቃሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት** ፡- በዚህ ክፍል ላይ እንደንግግር መነሻ እንዲሆናቸው የቀረበውን ምንባብ በግል እንዲያነቡ ያድርጉና ምንባቡን ካነበቡ በኃላ ተማሪዎቹን የንግግር (የመናገር) ሂደታቸውን እንዲቀጥሉ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎቹ ከርዕስ እንዳይወጡ ይጠብቋቸው፡፡ በየመሀሉ እንዴት እንደሚናገሩ ፍንጭ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለትምህርት ሦስት** መምህር ይህን ክፍለ ትምህርት ሲያስተምሩ ቅድመ ንባብ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅድሚያ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቃል ያሰሯቸው፡፡በመቀጠልም ንባቡን በግል እንዲያነቡ ያድርጓቸው፡፡ ቢቻል በደንብ እንዲያነቡት ጊዜ ይስጧቸው፡ ፡ከዚያም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሁለት ሁለት (በጥንድ ) በመሆን እንዲሰሩ ያድርጓቸው (እንደአስፈላጊነቱ

የራስዎን ዘዴ ሊጠቀሙ ይችላሉ) ከላይ ባነበቡት መሰረት ተመሳሳይ ምንባብ አዘጋጅተው እንዲመጡና ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት** ተማሪዎችን የሚያስተምሯቸው የደብዳቤ አፃፃፍ ስለሆነ፡፡ ስለግል ደብዳቤ ተማሪዎች የሚያውቁት ነገር ካለ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠልም በማስታወሻ ላይ የተገለፀውን ማብራሪያ ቀለልና ሰፋ አድርገው ይግለጹላችው፡፡ በመቀጠልም የደብዳቤውን ክፍሎች በደንብ ያስተምሯቸውና በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩት ያድረጉ የቀረበውን ሞዴል አፃፃፍ መሰረት አድርገው ሌላ ደብዳቤ ጽፈው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡

ቀን ------------

የተቀባይ አድራሻ

የላኪ አድራሻ--------------

---------------------------------------------------------------------------------

መግቢያ--------------------------------------------------------------------------- --------

ዋና መልዕክት ------------------------------------------------------------------------------

መደምደሚያ ……………………………………………………………….

ስምና ፊርማ --------------------

**ክፍለትምህርት አምስት (ቃላት)** በዚህ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሯቸው ቃላትን ስለሆነ የተጠቀሱትን ቃላት ከማስተማርዎ በፊት ስለአለፈው የቃላት ትምህርት ይከልሱላቸው፡፡ ከዚያም የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ በመቀጠልም በግላቸው የማዛመዱን ተግባር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት** (ስዋስው) ይህንን ክፍል ሲያስተምሩ ለማስተማሪያ የሚሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን ያዘጋጁ፡፡እነዚህን ዓረፍተ ነገሮች በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ስለ አረፍተ ነገር ዓይነቶች ያለማምዷቸው፡፡ ከዚያም የቀረበውን ማስታወሻ አንብበው የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ በመቀጠልም ሀተታዊና ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገርን በምሳሌው መሰረት ደጋግመው ያስረዷቸው፡፡ በመጨረሻም በቡድንም ይሁን በጥንድ የክፍል ሥራውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፧

**ክፍለ ትምህርት ሰባት(ሥነ-ጽሑፍ)** በዚህ ክፍል ግጥምን እንዴት እንደሚያነቡ የሚያስተምሩበት ስለሆነ ደግመው ደጋግመው እንዲያነቡ ከማድረግዎ በፊት እርሶ አንብበው ያሳዩአቸው፡፡በመቀጠልም ያንን ተከትለው እንዲያነቡ ያድርጉና ስለ ስንኝና ሀረግ ያሰተምሩአቸው፡፡ በመጨረሻም የቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

**ከፍለ ትምህርት ስምንት፤-ነፃ** በመጀመሪያ በትልቅ ወረቀት ላይ ነጻ ምእላድና ጥገኛ ምእላድን ሰርተው በማምጣት እሱን መሰረት አድርገው ያስተምሯቸው። በመቀጠልም ነፃ ምዕላድን ብቻ መርጠው በማሳየት ስለሱ ያስተምሯቸው። በመቀጠልም ምሳሌውን ያሰሯቸው በመጨረሻም በጥንድ ሆነው ነፃና ጥገኛ ምዕላድን እንዲለዩ ያድርጉ።

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ** ፡- በመጀመሪያ ከዚህ በፊት የተማሩትን የመጠይቃዊ ቃላት ትምህርት ባጭሩ ይከልሱላቸው። ከዚያም ምሳሌውን መሰረት አድርገው ጥያቄውን እራሳቸው እንዲሰሩ ያድርጉ (ስራው በቡድን ቢሆን ይመረጣል) ።

**ግምገማ**

- **አጭር ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎች**
- ቤት ወስድ ስራ
- የቡድን ስራ
- ጥያቄና መልስ
- ምልከታ
- የጽሁፍ ፈተና
- የቃል ጥያቄ
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄ

**ከፍለትምህርት አምስት**

**ቃላት**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በመመልከት ቀጥተኛ ፍች ስጡ።**

1. ሀሩር ከባድ ፀሐይ

2. አሽከር አገልጋይ

3. ክርክር ሙግት

4. ሚርት ቢታ

5. ሲሳይ እድል

**ክፍለ ትምህርት ስምንት**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት አይታችሁ ነፃ ያልሆነውን ለዩ፡፡**

| **<u>ነፃ ምዕላድ</u>** | **<u>ነፃ ያልሆነ ምዕላድ</u>** |
|---|---|
| 1. --------------------- | ወንድም |
| 2. -------------------- | ቤታችን |
| 3. ሰነፍ | -------------- |
| 4. ------------------------ | ግንበኛ |
| 5. ቆንጆ | ----------------- |
| 6. ሰፊ | ----------------- |

## ምዕራፍ ሰባት (9ክፍለ ጊዜ)

## ባህል

### ከዚህ ምዕራፍ በኂላ ተማሪዎች

- በሞባይል የተቀረፁ ታሪኮችን አዳምጠው ታሪኩን መልሰው ይናገራሉ፡፡
- ባሕላዊ መረጃን በትክክል ለክፍል ይናገራሉ፡፡
- ምንባብ አንብበው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ይገልጻሉ፡፡
- የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የአረፍተነገር ስልቶችን  አውቀው ይጽፋሉ፡፡
- የግጥም አላባውያንን ለይተው ያወጣሉ፡፡

### ዝርዝር አላማዎች

### ክፍለ ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ፡

- በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡
- አዳምጠው የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡

### ክፍለ ትምህርት ሁለት፡- መናገር

- ስለ አንድ ባህል መረጃ ሰብስበው ያቀርባሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት፡- ማንበብ**

- ምንባቡን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡
- ስለባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት በቅደም ተከተልይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት፡- መጻፍ**

- አንቀጽን በማስፋፋት ይጽፋሉ፡፡
- በምሳሌ፣ በማነጻጸርና በማወዳደር አንቀጽን ያስፋፋሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት አምስት፡- ቃላት**

ለቃላት ከአገባባቸው አንጻር ፍች ይሰጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡- ስሞች**

የተወሳጠ ስሞችን አጠቃቀም አውቀው ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡- ሰዋሰው**

- የአረፍተ ነገር ስልቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት፡- የግጥም አላባውያን**

- የስንኝን ምንነት ያብራራሉ፡፡
- ከስንኝ ውስጥ ሐረግን ያወጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡- ምሳሌያዊ ንግግር**

- ምሳሌያዊ ንግግርን ተጠቅመው ሃሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡

**<u>ዝርዝር ይዘት</u>**

**ክፍለ ትምህርት አንድ፡- ማዳመጥ**

- የተቀረጹ ታሪኮች (በሞባይል)

- አዳምጦ መናገር

**ክፍለ ትምህርት ሁለት፡- መናገር**

- ባህላዊ መረጃ መሰብሰብና ለክፍል መናገር

**ክፍለ ትምህርት ሦስት፡- ማንበብ**

- ምንባብ
- ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት

**ክፍለ ትምህርት አራት፡- መጻፍ**

- አንቀጽ ማስፋፋት
- በምሳሌ ማስፋፋት
- በማነጻጸርና በማወዳደር ማስፋፋት

**ክፍለ ትምህርት አምስት፡- ቃላት**

-

- አገባባዊ ፍች

**ክፍለ ትምህርት ስድስት፡- ስሞች**

- ተወላጠ ስሞች

**ክፍለ ትምህርት ሰባት፡- ሰዋሰው**

- የአረፍተ ነገር ስልቶች

**ክፍለ ትምህርት ስምንት፡- የግጥም አላባውያን**

- ስንኝ
- ሐረግ

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ፡-**

- ምሳሌያዊ ንግግር

<u>የትምህርቱ አቀራረብ</u>

**ክፍለ ትምህርት አንድ** (ማዳመጥ)፦ እባክዎትን መምህር በመጀመሪያ አንድ ወይም ሁለት ታሪኮችን በሞባይል ቀርጸው ያዘጋጁ። በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን ከማስደመጥዎ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ቀጥለው ታሪኩን ያስደምጡ። ታሪኩን ካስደመጡ በኋላ ማዳመጣቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ባዳመጡት ታሪክ መሠረት ስለ አንድ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር መረጃ በማሰባሰብ በሞባይል ቀርጸው እንዲያመጡና ለጓደኞቻቸው እንዲያስደምጡ ያድርጉ።

**ክፍለ ትምህርት ሁለት-** ( መናገር)፦ እባክዎትን መምህር ስለ ባሕል መረጃ ማብራሪያ ከመስጠትዎ በፊት የቅድመ መናገር ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ከዚያም በቡድን ያደራጁዋቸውና ስለሚያውቁት ባሕል እንዲወያዩ ያድርጉ። ከውይይት በኋላ የድህረ ንግግር ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

**ክፍለ ትምህርት ሦስት-** (ማንበብ)፦ መምህር እባክዎትን ምንባቡን ከማንበብዎ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።የቀደመ ዕውቀታቸውን ለመቀስቀስ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀሙ። ምንባቡን ሲያነቡ በትክክል ማንበባቸውንም ይከታተሉ። ከምንባቡ በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ስለሚያውቁት ብሔረሰብ ባሕላዊ የምግብ አዘገጃጀት እንዲጽፉና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

## የኮንታ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት

" ሱልሶ" " ኡስታ" ጫዲያ፣ " ኩቦ"፣ " በሩዋ" እና " ባጭራ" የኮንታ ብሔረሰብ ዋነኛ ባህላዊ ምግቦች ናቸው። " ሱልሶ" ከጥሬ ሥጋ፣ ከቅቤ ፣ ከደም ፣ ከሐሞት እና ከተለያዩ የማጣፈጫ ቅመሞች ከተዘጋጀ በኋላ በተለበለበና ክብ በተቆረጠ የእንሰት ቅጠል ላይ ለቤተሰቡ አባላት ይቀርብና በቡላ ወይም በቆጮ ይበላል። "ሱልሶ" ከቅቤና ከአይብ የሚዘጋጅ ሲሆን ለቤተሰቡ አባላት በቡድን ይቀርባል። "

ኡስታ" ከስጋ ከእንሰት ተዋጽኦዎች ከተለያዩ የእህል አይነቶች ከጎመን፣ ከቆጮ ከበቆሎ ዱቄትና እሸት አተር ይዘጋጃል፡፡ " ጫዲያ " የሚዘጋጀው ከተቀቀለ ጎደሬ ሲሆን በእንጨት ገበታ ተዘርግፎ እንዲቀዘቅዝ ከተደረገ በኋላ በመጨፍለቂያ ወይም በጫዶ ሚታ ተቀጥቅጦ ከተጨፈለቀ በኋላ በአይብና በወተት እየተጠቀሰ ይበላል፡፡ " ኩቡዋ " ከዶሮ ስጋ በተለየ ሁኔታ የሚሰራ የብሔረሰቡ ታዋቂ ምግብ ነው፡፡ " ቦሩዋ " ከበቆሎ ፣ ከጤፍ ፣ ከስንዴና ከአጃ ዱቄት የሚዘጋጅ ነው፡፡ " ባጭራ" ከተነከረ ቡላ ከአይብ ወይም ከአሬራ ወተት የሚሠራ ሲሆን ቅቤ ተጨምሮበት የሚበላ የምግብ አይነት ነው፡፡

**/ ምንጭ፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ኘሮፋይል/**

**ተግባር 1. ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡**

ሀ. የኮንታ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ፣ የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

ለ. ከቅቤና ከአይብ የሚዘጋጅ ምግብ የትኛው ነው?

ሐ. " የጫዲያ " ምግብ አዘገጃጀት የሚሰራው ከምንድነው?

መ. በወተትና በአይብ እየተጠቀሰ የሚበላው የምግብ አይነት የቱ ነው?

**ተግባር2 . ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. " የሱልሶ" ምግብ የሚዘጋጀው ከጥሬ ሥጋና ከቅቤ ብቻ ነው፡፡

ለ. ከተቀቀለ ጐደሬ የሚዘጋጀው ምግብ " ኩቡዋ " በመባል ይታወቃል፡፡

ሐ. "ቦሩዋ" የምግብ አዘገጃጀት ከበቆሎ ፣ ከጤፍ፣ ከስንዴና ከአጃ ዱቄት የሚዘጋጅ ነው፡፡

መ. "ኩቡዋ" ከዶሮ ሥጋ በተለየ ሁኔታ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው፡፡

**ተግባር3. ከ "ሀ" ሥር ያሉትን በ "ለ " ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡**

| **"ሀ"** | **"ለ "** |
|---|---|
| 1. "ሱልሶ" ፣ ጫዲያና ኡስታ፡፡ | ሀ. "ሲሊሶ" |
| 2. ከበቆሎ ዱቄትና እሸት አተር ይዘጋጃል ፡፡ | ለ. " ባጭራ" |
| 3. ከተነከረ ቡላና ከአይብ የሚዘጋጅ ፡፡ | ሐ. " ሱልሶ" |

4. ከሐሞት እና ከተለያዩ ማጣፈጫ ይዘጋጃል፡፡

መ.ባህላዊ የምግብ አይነቶች

5. ለቤተሰብ አባላት በቡድን የሚቀርብ፡፡

ሠ. "ኡስታ"

**ተግባር 1. የሚከተሉት አንቀጾች በምሳሌና በማነጻጸር የተስፋፉ ናቸው፡፡ እነዚህን በማንበብ ግንዛቤ ጨብጡ፡፡**

1. **በምሳሌ የተስፋፋ**

የኮሬ ብሔረሰብ በደቡብ ክልል የሚገኝ ሲሆን የብዙ ባህል ባለቤት ነው፡፡ ለምሳሌ ባህላዊ አስተዳደራቸው ፣ የጋብቻ ስነስርዓታቸው፣ የበዓላት አከባበራቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኮሬ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብ ለየት ያለ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ቁቹላ ፣ ገንፎ፣ ባራቂጣ፣ አንጩሳ የበሬ ስጋ ተከትፎ ተጠራቅሞ ከቆየ ወተት ጋር የሚሠራ፣ ኮይቻ፣ ሥጋ ተከትፎ በቆጮ መካከል ተደርጎ የሚበላው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2. **በማነጻጸር የተስፋፋ**

የኤሌክትሪክ ምጣድና የእንጨት ምጣድ ያላቸው ልዩነት በጣም ብዙ ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ምጣድ ጭስ የለውም፣ ሙቀቱም እንደ እሳት አይገርፍም፣ እንጨት መጨመር መቀነስ የሚባል የለበትም፡፡ የእንጨት ምጣድ ግን፣ ጭሱ፣ የእሳቱ ወላፈን፣ የምንጠቀመው እንጨት (እርጥብ፣ ደረቅ) ሰፊ ችግር ያለበት ነው፡፡

**ተግባር1. ቀጥለው በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. እጅግ አስከፊ ኑሮና ፈተና ገጥሟቸዋል፡፡
2. ይበልጥ ያሰሰባት የወንድሟ እንግልት ነበር፡፡
3. የስነ ልቦና ባለሙያ ምክር ተቀብለዋል፡፡
4 .ከነበሩበት የጎዳና ህይወት ተላቀቁ፡፡
5 ከእኩዮቻቸው ጋር መቦረቅ አልቻሉም፡፡
6. ለምለምና ዘላለም ተስፋቢስ ሆነው አልቀሩም፡፡

7. ከባድ የስራ <u>ሸክም</u> ተጫነባቸው፡፡
8  የስራ ድርሻ ወይም <u>አስተዋጽኦ</u> ነበራት፡፡
9  <u>አርአያ</u> መሆን ያስፈልጋል፡፡
10 ጎጂ <u>ልማዳዊ</u> ድርጊቶችን እንግታ፡፡

**ተግባር2. ከላይ በሠራችሁት መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

ሀ. ትውልድ

ለ. ሱስ

ሐ. ሀብት

መ. ለጋስ

ሠ. ደላላ

**ተግባር1. ቀጥለው የቀረቡትን ተውላጠ ስሞች በደንብ ተመልክታችሁ አገልግሎታቸውን ተረዱ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| እኔ | አንተ | እናንተ | እሷ |
| እኛ | አንቺ | እነሱ | እሱ |

**ተግባር2. ከላይ ከቀረቡት ተውላጠ ስሞች በመምረጥ የተሰመረባቸውን ስሞች ተኩ፡፡**

1. <u>ደጊቱ</u> ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡
2. <u>አለሚቱና አበበ</u> ተማሪዎች ናቸው፡፡
3. <u>እኔና ወንድሜ</u> ስለሀገራችን እናስባለን፡፡
4. <u>ተሾመ</u> ለልጆቹን ምክር ይመክራቸዋል፡፡
5. <u>አንቺና አለሙ</u> ነገ ትመጣላችሁ፡፡
6. <u>አማረ</u> የቤት ስራውን ቶሎ ቶሎ ይሰራል፡፡

**ተግባር3. ከላይ በተማራችሁት መሠረት ቀጥሎ በቀረቡት ተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

1. እኔ                5. እሱ

2. አንተ
3. እሷ
4. እነሱ
6. እናንተ
7. እኛ
8. አንቺ

**ተግባር4 – ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመመልከት ቀጥለው የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ትዕዛዛዊ ወይም አጋናኝ በማለት መልሱ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ እንዳትነካ፡፡ - ትዕዛዛዊ

ለ. ፈረስ የሚያስጋልብ ቤት፡፡ - አጋናኝ

1. አለምን ያስደመመ ንግግር፡፡
2. ሰዓት ሳይደርስ ከክፍል አትውጡ፡፡
3. በጣም የምትገርም ጎል!
4. ወጧ እጅ ያስቆረጥማል፡፡
5. ማስክ ሳታደርግ ከቤት አትውጣ፡፡
6. የቤት ስራውን ሰርታችሁ አምጡ፡፡
7. ጩኸቱ ምድር ያናውጣል፡፡
8. ምግብ ከመብላትህ በፊት እጅህን ታጠብ

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀርበውን ምሳሌ በቡድን በመሆን አንብቡና ተረዱት፡፡**

**ስንኝ የግጥም አንድ መስመር ነው**

**ምሳሌ፡-**

አይዞህ የኔ ጌታ ነገርህን አርትሳ (ስንኝ)1

አለስልሰህ ዝራ የስንዴውን ማሳ፡፡ (ስንኝ)2

በዚህ ግጥም ውስጥ ሁለት ስንኞች አሉ ማለት ነው፡፡

**ሀረግ፡- የስንኝ እኩሌታ ሆኖ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ነው፡፡**

**ምሳሌ፡-**

ቅሰሙ ወጣቶች ፣ጥበብን ተግታችሁ፣

ስንፍና በፍፁም ፣አይግባ ልባችሁ፣

**ተግባር2. ከላይ በተመለከትነው ግጥም ውስጥ ሁለት ስንኞችና አራት ሐረጎች አሉ። በዚሁ መሰረት ቀጥሎ ከቀረበው ግጥም ስንኞችንና ሃረጎችን አውጡ።**

አርሶ መሸመት ፣ተኩሶ መሳት፣
ይለበልባል፣ እንደ እግር እሳት።
አረንዛ ውጦኝ፣ እስከ ጉልበቴ፡
ሽልም አወጣኝ ፣የነፍስ አባቴ።
ያላረሰ ጎበዝ ፣እርፍ ያልነቀነቀ፡
ስልቻውን ይዞ፣ ለቃርሚያ ዘለቀ።

1. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

ሀ. 10 ለ. 8 ሐ. 6 መ. 4

2. ግጥሙ ስንት ሀረጎች አሉት?

ሀ. 12 ለ. 14 ሐ. 16 መ. 18

3. ግጥሙ ስንት መነሻ ሀረጎች አሉት?

ሀ. 4 ለ. 6 ሐ. 8 መ. 10

1. የግጥሙ አንድ ስንኝ ስንት ሐረግ አለው?
2. ሀ. 10 ለ. 8 ሐ. 6 መ.4

**ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማንበብ በምን በምን ጉዳይ ላይ እንደተነገሩ ወይም ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ በጽሁፍ መልሱ።**

1. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ - ጥንቃቄን
2. ስጋ በልቶ ከብስና ጎመን በልቶ በጤና።
3. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ።
4. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ።
5. እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች።
6. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ።
7. ለሰው ብሎ ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ።

8. ሀሜትና ጅራት ከበስተ ኋላ ነው፡፡

**ተግባር2. ቀጥለው በቀረቡት ሁኔታዎች ዙሪያ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አዘጋጅታችሁ / ጽፋችሁ በማምጣት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. መቸኮል መጥፎ እንደሆነ
2. ሴቶችን የሚያሞግሱ
3. መስራትን የሚያበረታቱ
4. ኃላፊነትን የሚነግሩ

**ክፍለ ትምህርት አራት** - መጻፍ፡- ስለ አንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴ ጥቂት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን ተጠቅመው አንቀጽ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው በምሳሌ በማስደገፍ ያሳዩአቸው፡፡ በምሳሌው መሰረት በምሳሌ ፣ በማነጻጸርና በማወዳደር ስልት አንቀጽ ጽፈው እንዲያመጡ ያድርጉ፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት-** ቃላት፡- የቃላት አገባባዊ ፍችን በሚያስተምሩ ጊዜ ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ከቀጥተኛ ፍች የተለየ ፍች እንደሚኖራቸው ይንገሯቸው፡፡ ለሚሰጧቸው መልመጃ ለቃላቱ ትክክለኛ አገባባዊ ፍች መስጠታቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት- ተውላጠ ስሞች፡-** እባክዎትን መምህር ስለተውላጠ ስም ምንነትና አገልግሎታቸውን በሚመለከት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ስሞችን በተውላጠ ስም እየተኩ እንዲሰሩና በተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት- ሰዋሰው**፡-በመጀመሪያ ስለአረፍተነገር አይነቶች ይንገሯቸው፡፡በመቀጠልም ስለ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገርና ስለ አጋናኝ አረፍተ ነገር አጠር ያለ ገለጻ ያድርጉላቸውና መልጃዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት - ግጥም**፡ከግጥም አላባውያን ስለ ስንኝና ስለ ሐረግ ምንነት ይንገሯቸው፡፡ ግጥም በማቅረብ የግጥሙን ስንኝና ሐረግ ያሳዩአቸው፡፡

በመቀጠልም ከቀረበው ግጥም ውስጥ ሐረግና ስንኙን በትክክል ለይተው መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ** - ስለምሳሌያዊ ንግግር ምንነት ገለጻ ያድርጉ፡፡ የተለያዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በማቅረብ የያዙትን መልዕክት ይንገሩ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ ስለተለያዩ ሁነቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ጽፈው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡

***መርጃ መሳሪያ***

- በሞባይል የተቀረፁ ታሪኮች
- በፅሁፍ የቀረበ ግጥም
- ምሳሌያዊ ንግግሮች

**ግምገማ/ምዘና/**

- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ስራ
- ጥያቄና መልስ
- የግል ስራ
- የጽሁፍ ፈተና
- የቃል ጥያቄ
- የቡድን ስራ
- የተግባር ጥያቄ
- የቃል ጥያቄ

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

**ተግባር 1 ቀጥለው በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ውጣ ውረድ
2. ችግር
3. የማማከር አገልግሎት
4. ኑሮ
5. መደሰት
6. ተስፋ የሌለው
7. ጫና
8. ድጋፍ
9. ምሳሌ
10. ባህላዊ

ክፍለትምህርት ስድስት

**ተግባር 2 ከላይ ከቀረቡት ተውላጠ ስሞች በመምረጥ የተሰመረባቸውን ስሞች ተኩ፡፡**

1 እሷ

2.እነሱ

3.እኛ

4.እሱ

5.እናንተ

6.እሱ

**ክፍለትምህርት ዘጠኝ ተግባር** 1 ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማንበብ በምን በምን ጉዳይ ላይ እንደተነገሩ ወይም ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1.ጥንቃቄን

2.ጥንቃቄን

3.ችኮላን

4.ስንፍናን

5.ይሉኝታ ማጣትን

6.እራስ ወዳድነትን

7.ጥንቃቄን

8.ስለራስ አለማወቅን

**ምዕራፍ ስምንት-** **(9ክፍለ ጊዜ)**

## መቻቻል

ከዚህ ምዕራፍ በኂላ ተማሪዎች

- በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን አዳምጠው ስላዳመጡት ባህል ጠንካራና ደካማ ጎን ይናገራሉ፡፡
- ቀለል ስላሉ የመስክ ጉዞዎች ይናገራሉ፡፡
- ገላጭ ምንባቦችን አንብበው ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡
- የድርሰት አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- ለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፡፡
- መቼትና ዋና ገጸ ባህሪያትን ለይተው ያወጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አንድ- ማዳመጥ፡-**

- በሞባይል ተቀርጾ የሚቀርብላቸውን ንግግር አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት- መናገር፡-**

- በመስክ ጉዞ ላይ የተመለከቷቸውንና የሰበሰቧቸውን መረጃዎች በቃል ለክፍል ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት -ማንበብ**

- ተቻችሎ መኖር እንዴት እንደሆነ ከምንባቡ ተረድተው ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት- መጻፍ፡-**

- የድርሰት አጻጻፍን አውቀው ድርሰት ይጽፋሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት- ቃላት፡-**

- ለቃላት እማሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የቃላትን ፍካሬያዊ ፍች ያወጣሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት -ስዋስው**

**- የቃል ክፍሎች፡-**

- ስምን በዐረፍተነገር ውስጥ በትክክል ያስገባሉ፡፡
- የቅጽሎችን  አገልገሎት ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት- ስነ- ጽሁፍ፡-**

- ከልቦለድ ውስጥ ዋና ገጸ ባሕሪያትን ያወጣሉ፡፡
- የልቦለዱን መቼት ይናገራሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት፡- የቃል ክፍሎች፡-**

- አምስቱን የቃል ክፍሎች ይዘረዝራሉ፡፡
- መስተዋድድና ተውሳከ ግስን ተጠቅመው ዐረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች**

**ክፍለ ትምህርት አንድ- ማዳመጥ፡-**

- የተቀረጹ አገር በቀል ዕውቀቶችን ማዳመጥ

**ክፍለ ትምህርት ሁለት - መናገር**

- የመስክ ጉዞ

**ክፍለ ትምህርት ሦስት- ማንበብ፡-**

- ምንባብ
- ተቻችሎ መኖር

**ክፍለ ትምህርት አራት- መጻፍ፡-**

- የድርሰት ክፍሎች
- ድርሰት መጻፍ

**ክፍለ ትምህርት አምስት - ቃላት፡-**

- እማሬያዊ ፍች
- ፍካሬያዊ ፍች

**ክፍለ ትምህርት ስድስት - ሰዋስው፡-**

- ስም
- ቅጽል

**ክፍለ ትምህርት ሰባት - ስነ- ጽሁፍ፡-**

- ዋና ገጸ ባህሪ
- መቼት

**ክፍለ ትምህርት ስምንት- ስዋስው**

- መስተዋድድ
- ተውሳከ ግስ
- ግስ

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ ቃላት**

- የቃላት ቀጥተኛ ፍች


**<u>የትምህርት አቀራረብ</u>**

**ክፍለ ትምህርት አንድ-- ማዳመጥ፡-** መምህር ንግግሩን ከማስደመጥዎ በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ እባኮትን መምህር አሁን በሞባይል የተቀዳውን ንግግር ያስደምጧቸው፡፡ ንግግሩን ካስደመጡ በኋላ በትክክል ማዳመጣቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡ (ያሰሯቸው)፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሁለት - መናገር**፡- አባክዎትን መምህር ስለ መስክ ጉዞ ምንነት በአጭሩ ያብራሩላቸው፡፡ የመስክ ጉዞ ሲያደርጉ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም የመስክ ጉዞ እንዲያደርጉና በመስክ ጉዞው ላይ ያገኙትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት - ማንበብ**፡- ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ይቀስቅሱ፡፡በመቀጠልም ምንባቡን ያንብቡ፡፡ በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ፡፡ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችንም በትክክል መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አራት- መጻፍ**፡- ስለ ድርሰት ምንነትና ስለ ድርሰት ክፍሎች በደንብ ይንገሯቸው፡፡ በተነገራቸው መመሪያ መሠረት ከሚሰጧቸው ድርሰት ውስጥ በትክክል የድርሰት ክፍሎችን ለይተው ማውጣታቸውንና አንቀጽ መጻፋቸውን ያረጋግጡ፡፡




**ክፍለ ትምህርት አምስት- ቃላት**፡- ስለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ምንነት ይንገሯቸው፡፡ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስድስት- ስዋሰው**፡- በዚህ ክፍል ስለስምና ስለ ቅጽል ምንነት አጠር ያለ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡በመቀጠልም የተለያዩ ቃላትን በመስጠት በየቃል

ክፍሉ በማስቀመጥ ያሳዩ ፡፡በመጨረሻም ለተማሪዎቹ የተለያዩ ቃላትን በመስጠት በየቃል ክፍሉ ማስቀመጣቸውን ይከታተሉ፡፡

**<u>ክፍለ ትምህርት ሰባት</u>- <u>ስነ- ጽሑፍ</u>፡-** በዚህ ክፍል ከልቦለድ አላባውያን ውስጥ ገጸባህሪና መቼት ቀርቧል፡፡ በልቦለድ ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባር ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ የተመረጡ የልቦለድ ክፍሎችን በመውሰድ ገጸባህሪንና መቼትን በደንብ ለይተው እንዲያውቁ ያድርጉ፡፡ ለተማሪዎቹም ተቀንጭቦ የተወሰደ ልቦለድ በመስጠት ከዚያ ልቦለድ ውስጥ ገጸባህሪንና መቼትን ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡በትክክል መስራታቸውንም ያረጋግጡ፡፡

**<u>ክፍለ ትምህርት ስምንት፡-</u>** በዚህ ክፍል ከቃል ክፍሎች ውስጥ መስተዋድድ፣ ተውሳከ ግስ እና ግስ ተካተዋል፡፡ በማስቀደም ምንነታቸው ይንገሩ፡፡ በመቀጠልም ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው፡፡ የሚሰጧቸውን ቃላት በየቃል ክፍሉ መጻፋቸውን ያረጋግጡ፡፡

**<u>ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ</u>፡-** ስለ ቃላት ቀጥተኛ ፍች ምንነት አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡ የሚሰጧቸውን ቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡

***<u>መረጃ መሣሪያ፡-</u>***

- የተቀረፁ አገር በቀል ታሪኮች
- ድርሰት
- የልቦለድ መጽሐፍ

## ምዘና

-የጽሁፍ ስራ

- ጥያቄና መልስ
- የድርሰት ግምገማ
- ግለ ገለጻ ፣ የቡድን ስራ
- የቡድን ስራ
- የመረዳት ጥያቄ

## በናሙናነት ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ

## ክፍለ ትምህርት አምስት

**ተግባር 2 ከላይ በተመለከታችሁት ምሳሌ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የሚሰጧችሁን ቃላት እማሬያዊ ፍች**

ሀ. እባብ- ተናደፊ

ለ. አህያ - የቤት እንስሳ

ሐ. አሣማ - ለማዳ እንስሳ

መ. ነቀዝ - የእህል ውስጠኛውን ክፍል የሚበላ

ሠ. ቀዳዳ - የተበሳ

ረ. ሚጥሚጣ - የበርበሬ ዘር

ሰ. መሬት - የሰዎች መኖሪያ

ሸ. ሬሳ - በድን / የሞተ/

ቀ. ምስጥ - የምድር ነፍሳት

በ. ክብሪት - የእሳት ማቀጣጠያ

**ተግባር 3 ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃላት ፍካሬያዊ ፍች ጻፉ፡፡**

**ሀ. ነቀዘ - ሳይታወቅ የሚጎዳ**

ለ. እሳት - ፈጣን/ጎበዝ

ሐ. ወንፊት -ወሬ የማይቋጥር/ምስጢር የማይጠብቅ

መ. ውሻ - ልክስክስ

ሠ. ዱባ - ወፍራም

ረ. ጅብ - ብቻውን የሚበላ / ሆዳም/

ሰ. ጩሉሌ - ብልጥ

ሸ. ገለባ - ቀላል /ወራዳ/

ቀ. ጆሮ - ወሬ አቀባይ

**ክፍለትምህርት ስድስት**

**ተግባር 3 በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ/ ቅጽል

ለ/ ቅጽል

ሐ/ስም

መ/ ስም

ሠ/ቅጽል

ረ/ ስም

**ክፍለትምህርት ስምንት ተግባር 2 ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች እንደተረዳችሁት ቀጥለው ከቀረቡት ቃላት ውስጥ መስተዋድዶችን ለብቻ ተውሳከ ግሶችን ለብቻ ግሶችን ለብቻ በቡድን በመሆን ለዩ፡፡**

| መስተዋድድ | ተውሳከግስ | ግስ |
|---|---|---|
| ወደ | ምንኛ | ነበር |
| በ | ነገ | ሸጠው |
| ከ | | አገኘሁ |
| | | መጡ |
| | | ለመደ |

**ምእራፍ ዘጠኝ (9 ክፍለጊዜ)**

## ተላላፊ በሽታዎች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች አዳምጠው ይመልሳሉ፡
- ኮሮና ቫይረስ የሚተላለፍባቸውን መንዶች ያብራራሉ፡፡
- ተራኪ ምንባቦችን አንብበው ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡
- ተራኪ የሆኑ ድርሰቶችን ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የስርወ ቃልን ምንነት ይረዳሉ፡፡
- የልቦለድ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ስማዊ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡

**ዝርዝር አላማዎች**

**ክፍለ ትምህርት አንድ- ማዳመጥ፡-**

- የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች አዳምጠው ይመልሳሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት ሁለት- መናገር፡-**

- ስለ ኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶች ያውቃሉ፡፡
- ኮሮና ቫይረስ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ይረዳሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት- ማንበብ፡-**

- የቀረበውን ምንባብ አንብበው ይረዳሉ፡፡
- የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን አውቀው ይናገራሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት አራት- መጻፍ፡-**

- ስለ ተራኪ ድርሰት ምንነት ያውቃሉ፡፡
- አንድ ርዕስ መርጠው ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት አምስት- ቃላት፡-**

- ለቃላት እማሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ፍካሬያዋ ፍች ይሰጣሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት ስድስት - ሰዋሰው፡-**

- ስለ ስርወ ቃል ምንነት ያውቃሉ፡፡
- ከቃል ውስጥ ስርወ ቃልን ያወጣሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት ሰባት- ስነ ጽሁፍ፡-**

- የልቦለድ ምንነት ያውቃሉ፡፡
- የልቦለድ አይነቶችን ይናገራሉ፡፡
-

**ክፍለ ትምህርት ስምንት-**

- የስማዊ ሐረግን ምንነት ይረዳሉ፡፡
- ስማዊ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ- ግጥም፡-**

- ከግጥም ውስጥ ስንኝና ሀረጎችን ቆጥረው ያውቃሉ፡፡

**ዝርዝር ይዘቶች**

**ክፍለ ትምህርት አንድ**

- አጻምጦ ጥያቄ መመለስ

**ክፍለ ትምህርት ሁለት**

- ኮሮና ቫይረስ

**ክፍለ ትምህርት ሦስት**

- ኮሮና ቫይረስ የሚተላልፍባቸው መንገዶች

**ክፍለ ትምህርት አራት**

- ተራኪ ድርሰት
- ተራኪ ድርሰት መጻፍ

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

- እማሬያዊ ፍቾ
- ፍካሬያዊ ፍቾ

**ክፍለ ትምህርት ስድስት-**

- ስርወ ቃል
-

**ክፍለ ትምህርት ሰባት- ስነ ጽሁፍ፡-**

- የልቦለድ አይነቶች

**ክፍለ ትምህርት ስምንት- ስማዊ ሀረግ፡-**

- ስማዊ ሀረግ

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ- ግጥም፡-**

- ስንኝና ሐረግ መለየት

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ክፍለ ትምህርት አንድ - ማዳመጥ፡-መምህር እባክዎት በመጀመሪያ የተዘጋጀውን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጓቸው ፣በመቀጠልም የቀረበውን ምንባብ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡**

**ተላላፊ በሽታዎች**

ተላላፊ በሽታ የምንለው ከሰው ወደ ሰው ፣ከእንስሳ ወደ እንስሳ ፣ የሚተላለፍ በሽታ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በሽታው ካለበት ወደ ሌለበት በመነካካት፣ በትንፋሽ ፣ በልብስ ፣ ወዘተ .. የሚተላለፍ ስለሆነ ነው፡፡ በትንፋሽ ከሚተላለፉ በሽታዎች መካከል ሳንባ ነቀርሳ፣ ኮሮና ቫይረስ፣ ጉንፋን ፣ ወዘተ.. ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በግብረ ስጋ የሚተላለፉ ኤች አይቪ ኤድስ ፣ ጨብጥ፣ ወዘተ… ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከዚህም ውጪ በተለያየ መንገድ የሚተላለፉ በውሃ ፣ በምግብ፣ ወዘተ … በሽታዎች አሉ፡፡

በአጠቃላይ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች ለሕይወት አደጋ ስለሚሆኑና እስከ ሞትም ስለሚያደርሱ ጥንቃቄ ልናደርግባቸው ይገባናል፡፡ በተለይ በአሁኑ ሰዓት ኮሮና ቫይረስ በከፍተኛ ደረጃ ሕይወት እያጠፋ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል፡፡ በተለይ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ተሰብስባችሁ ስለምትማሩ ከተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሁለት- መናገር፡-

እባኮትን መምህር ለተማሪዎች ስለ ኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችና ቫይረሱ የሚያስከትላቸውን ችግሮች ሰፋ አድርገው ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም ተማሪዎቹ ስለ ኮሮና ቫይረስ አስከፊነት እንዲናገሩ ያድርጉ። ኮሮና ቫይረስን ለመከላከል የሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲወያዩና እንዲነጋገሩ ያድርጉ።

## ክፍለ ትምህርት ሦስት- ማንበብ፡-

በዚሁ ክፍል ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን ከማስነበብዎ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ከምንባቡም በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

## ክፍለ ትምህርት አራት- መጻፍ፡-

መምህር በቅድሚያ ስለተራኪ ድርሰት ምንነት ይንገሯቸው።ከዚያም ለናሙናነት የቀረበውን ተራኪ ድርሰት አቀራረቡን በመንገር በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ርዕስ መርጠው ተራኪ ድርሰትን ጽፈው እንዲመጡና እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

## ክፍለ ትምህርት አምስት-

እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች፡-መምህር በመጀመሪያ ስለ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ምንነት ይንገሯቸው። በሚሰጧቸው ገለጻ መሰረት ለሚሰጧቸው ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠታቸውን ያረጋግጡ።

## ክፍለ ትምህርት ስድስት- ሰዋሰው፡-

በዚህ ክፍል ስለ ስርወ ቃል ቀርቧል። ስለስርወ ቃል ምንነት ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም በምሳሌ በማስደገፍ ከነማብራሪያው ገለጻ ይስጧቸው፡

፡ በተሰጣቸው ገለጻ መሰረት ከተሰጣቸው ቃላት ስርወ ቃልን ለይተው ማውጣታቸውን ይከታተሉ፡፡እርማትም ይሰጣቸው፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሰባት - ስነ ጽሁፍ፡-**

በዚህ ክፍል ልቦለድን የሚመለከት ነው፡፡ የልቦለድን ምንነትና የልቦለድን አይነቶች በምሳሌነት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ በተሰጣቸው ገለጻ መሰረት ለሚጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ መስጠታቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት- ስማዊ ሐረግ፡-**

በዚህ ክፍል ስማዊ ሐረግ ቀርቧል፡፡ ስለስማዊ ሐረግ ምንነትና ስማዊ ሐረግን የሚመለከቱ ሐረጎችን ያሳዩአቸው፡፡ የተለያዩ ቃላትን በመስጠት ስማዊ ሐረግን እየመሰረቱ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ- ግጥም፡-**

ስለስንኝና ስለ ሐረግ ምንነት ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም መምህር በጽሁፍ የተዘጋጀ ግጥም በማቅረብ ከግጥሙ ውስጥ ስንኝና እና ሐረግን ቆጥረው ለይተው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

***<u>መርጃ መሳሪያ</u>***

- ሞዴል ድርሰት
- በጽሁፍ የሚቀርብ ግጥም

**<u>ምዘና</u>**

- የቡድን ስራ
- ግለ ገለጻ
- ጥያቄና መልስ

- የጽሁፍ ፈተና
- ቃላዊ ጥያቄ
- የተግባር ፈተና
- የመረዳት ጥያቄ

**በናሙናነት የቀረቡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለ ትምህርት አምስት ተግባር 1 ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍች ስጡ፡፡**

| <u>**እማሬያዊ ፍች**</u> | <u>**ፍካሬያዊ ፍች**</u> |
|---|---|
| **ሀ/መኖሪያ** | **ትዳር** |
| **ለ/ የሚነድ** | **ብልጥ/ጎበዝ** |
| **ሐ/ቀደደ** | **አልደቀቀም** |
| **መ/ድንጋይ ለበስ እንስሳ** | **ቀርፋፋ** |
| **ሠ/ ለቤት መስሪያ የሚያገለገል** | **የማይገባው** |

**ክፍለ ትምህርት ስድስት ተግባር 1 ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ ተመልክታችሁ ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ስርወ ቃል አውጡ፡፡**

ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ ተመልክታችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ስርወ ቃል አውጡ፡፡

| <u>**ቃል**</u> | <u>**ስርወ ቃል**</u> |
|---|---|

1. ገደለ ግ-ድ-ል
2. ለቀመ ል-ቅ-ም
3. ሰቀለ ስ-ቅ-ል
4. ደከመ ድ- ክ-ም
5. ብልህ ብ-ል-ህ

**ክፍለ ትምህርት ስምንት ተግባር 3 ከዚህ በታች ከቀረቡ ቃላት ውስጥ ስም የሆነውን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

.ሀ. አስተማሪ መ. ሰው

ለ. ልጅ ሠ. ጫማ

ሐ. ቤት ረ. ስጋ

## ምዕራፍ አሥር (ክፍለጊዜ9)

### የፈጠራ ሥራ

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የፈጠራ ሥራዎችን አዳምጠው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፧
- በማህበራዊ ዐውዶች ሀሳባቸውን በአክብሮት ይገልፃሉ፡፡
- ከምንባብ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ያወጣሉ፡፡
- ገላጭ ድርሰትን አስተካክለው ይጽፋሉ፡፡
- ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ግሳዊ ሀረግን ያዋቅራሉ፡፡
- የአነፃፃሪ ዘይቤን ምንነት ያብራራሉ፡፧

**ዝርዝር ዓላማዎች**

**ክፍለትምህርት አንድ ማዳመጥ**

- ስለ ፈጠራ ስራ የቀረበላቸውን ምንባብ አዳምጠው ሃሳቡን አሳጥረው ይናገራሉ፡፡
- የፈጠራ ስራን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ሁለት መናገር**

- የአክብሮት ንግግርን አውቀው በአክበሮት ይናገራሉ፡፡
- ዐውዱን አይተው ንግግራቸውን ያስተካክላሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ሦስት አቀላጥፎ ማንበብ**

- ምንባቦችን አቀላጥፈው ያነባሉ፡፡

- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ዐውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡
- የምንባቡን መልዕክት ለክፍል ተማሪዎች ያካፍላሉ፡፡

**ክፍለትምህርት አራት መፃፍ**

- የገላጭ ድርሰትን ባህርያት ይዘረዝራሉ፡፡
- በገላጭ ድርሰት አንድ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት አምስት- የቃላት ተዛማጅ ትርጉም**

ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም ይሰጣሉ፡፧
- የቃላትን ተዛማጅ ትርጉም አውቀው ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለትምህርት ስድስት**

- ስዕሉን  ተመልክተው ያብራራሉ ፡፡
- ስዕሎችን ያነፃጽራሉ፡፡
- ስዕሎቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ይናገራሉ፡፡
-

**ከፍለ ትምህርት ሰባት - ሰዋሰው**

- የግሳዊ ሀረግን ምንነት በዝርዝር ይተነትናሉ፡፡
- ግሳዊ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡

**ከፍለ ትምህርት ስምንት**

- የቅጽሎችን ብዙ ቁጥር አውቀው ይጠቀማሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ ስነ -ጽሁፍ**

- የአነፃፃሪ ዘይቤን ባህርያት ያብራራሉ፡፡
- አነፃፃሪ ዘይቤን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

**ዝርዝር ይዘቶች**

**ክፍለ ትምህርት አንድ ማዳመጥ**

- ማዳመጥ
- ጥያቄዎችን መመለስ

**ክፍለ ትምህርት ሁለት**

- የአክብሮት (የትህትና) ንግግር
- አውዳዊ ንግግር

**ክፍለትምህርት ሦስት**

- ምንባብ
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች
- የምንባቡን መልዕክት ማውጣት

**ክፍለ ትምህርት አራት**

ገላጭ ድርሰት

**ክፍለ ትምህርት አምስት**

የቃላት ተዛማጅ ትርጉም

**ክፍለ ትምህርት ስድስት**

- ስዕልን ተመልክቶ መረዳት
- ስዕሎችን ማነፃፀር

**ከፍለ ትምህርት ሰባት**

ግሳዊ ሀረግ

**ክፍለትምህርት ስምንት**

- ቅጽል

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ**

- ዘይቤ

**የትምህርቱ አቀራረብ**

ክፍለትምህርት አንድ( ማዳመጥ) መምህር በመጀመሪያ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡በመቀጠልም ንባቡን ያንብቡላቸውና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

**የፈጠራ ስራዎች**

የፈጠራ ስራዎች የሚባሉት አይምሮአችንን ተጠቅመን የምናገኛቸው ግኝቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ግኝቶችም በተለያዩ ጉዳዩች ላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ለምሳሌ በጤና

ዙሪያ ፣በማህበራዊ ህይወት ዙሪያ ፣በኢኮኖሚ ዙሪያ ፣ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በገጠሩ አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ በኑሮው ወደኋላ የቀረ ነው። መብራት የለውም፣ ምግብ የሚያበስለውም በእሳት ነው። ለምግብነት የሚያገለግለውን እንስት የሚያዘጋጀው በኋለ ቀር መንገድ ነው። ስለዚህ ማህበረሰባችንን ከዚህ ችግር ለማውጣት፣ በዚህ ችግር ዙሪያ ምርምር ማድረግና የፈጠራ ስራዎችን መፍጠር ተገቢ ነው። እናንተም በአከባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮችን ተጠቅማችሁ የአከባቢያችሁን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ የፈጠራ ስራዎችን መስራት ይኖርባችኋል።

**ክፍለ ትምህርት ሁለት- መናገር** እባኮትን መምህር ለተማሪዎችዎ የአክብሮት( የትህትና) ንግግር ምን እንደሆነ ይንገሯቸው።በአውድ ውስጥ ንግግራቸውን እንዴት አስተካክለው እንደሚናገሩ በምሳሌ በማሳየት ሰፋ ያለ ገለፃ ይስጧቸው።

**ክፍለ ትምህርት ሦስት - አቀላጥፎ ማንበብ** በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ምንባብ ቀርቧል። ከምንባቡ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ምንባቡን በትክክል እያነበቡ እንደሆነ ይከታተሏቸው። ከምንባቡ በኋላ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

**ክፍለ ትምህርት አራት - መፃፍ** ፡በዚህ ክፍል ገላጭ ድርሰት ቀርቧል። ስለ ገላጭ ድርሰት ምንነት ገለፃ ያድርጉላችው። ከገለፃው በኋላ ለናሙና የተወሰደውን ገላጭ ድርሰት እንዲጽፉ (ሂደቱን) ይንገሯቸው። በነገሯቸው ገለፃ መሰረት ሌላ ገላጭ ድርሰት ጽፈው እንዲመጡ ያድርጓቸው።

**ክፍለ ትምህርት አምስት-** የቃላት ተዛማጅ ትርጉምን ምንነት በማስመልከት ምሳሌ በመስጠት ስለ ቃላት ተዛማጅ ትርጉም ይንገሯቸው። ቃላቱ የሚኖራቸውን ዝምድና በደንብ ያስረዷቸውና በተማሩት መሰረት ሌሎች ተዛማጅ ትርጉም ያላቸውን ቃላት ሰብስበው እንዲመጡ ያድርጓቸው።

**ክፍለ ትምህርት ስድስት** - መምህር በዚህ ክፍል ስዕል ቀርቧል፡፡ ስዕሉ የያዘውን መልዕክት ይንገሯቸው፡፡ ስዕሉን ከተመለከቱ በኋላ በስዕሉ ላይ ያለውን በማነፃፀር የተረዱትን መልዕክት (ያዩትን ነገር) እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

**ክፍለትምህርት ሰባት**- ስለ ግሳዊ ሀረግ ምንነት፣ ስለግሳዊ ሀረግ አመሠራረት ይንገሯቸው፡፡ በተማሩት መሰረት ግሳዊ ሀረግ መመሰረታቸውን ይከታተሉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ስምንት**- ስለ ቅጥያ ምንነት ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም ቅጽሎችን ወደ ብዙ ቁጥር እየቀየሩ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡ ባሳዩት መሰረት ቅጽሎችን ወደ ብዙ ቁጥር ቀይረው ሰርተው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ**- ስለ ዘይቤ ምንነት ይንገሯቸው፡፡ ከዘይቤ አይነቶች መካከል ስለ አነፃፃሪ ዘይቤ ምንነት ያስረዷቸውና ስለአነፃፀሪ ዘይቤ የሚገልፁ ምሳሌዎችን ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎችም በተሰጣቸው ምሳሌ መሰረት ሌሎች አነፃፀሪ ዘይቤዎችን ጽፈው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡

***<u>መርጃ መሳሪያ</u>***

**ስዕል**

**ምዘና**

- አሳታፊ ምዘና
- ምልከታ /ተግባራዊ ምዘና/
- የጽሁፍ ፈተና
- የተግባር ስራ
- የቡድን ስራ
- የቡድን  ስራ
- የመረዳት ጥያቄ

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ክፍለትምህርት አምስት**

ተግባር 1 ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተዛማጅ ትርጉማቸውን ተናገሩ፡፡

1. እውቀት - ብርሃን
2. ድንቁርና - ጨለማ
3. ችግኝ - ህፃን
4. አድባር - ባለግርማ/ ትልቅ
5. ልምላሜ - አረንጓዴ
6. ልጅ - ፍሬ
7. እናት - ሀገር
8. እርግብ - ሰላም

ክፍለትምህርት ሰባት

ተግባር 1 ከዚህ በታች የቀረቡ ምሳሌዎችን በመመልከት ቀጥሎ ከቀረቡት ሐረጎች ውስጥ ግሳዊ ሐረግን ለይታችሁ አውጡ፡፡

**ግሳዊ ሀረግ**

1.ኮፊያ አደረግ፡፡

2.እንጨት ሰበረ፡፡

3.ፈረስ ጋለበ፡፡

4 ወድቆ ተነሳ፡፡

5 ታሞ ሞተ፡፡

6 ወተት ጠጣ።

7 እንጀራ ጋገረች።

8 ልብሱን አጠበ።

9ትምህርት ቤት ሄደ።

# ዋቢ ጽሁፎች

*መስፍን ሀብተማርያም*፡፡(1996-1999)፡፡ *የቡናቤት ሰዕሎች ና ሌሎች ወጎች፡፡* አዲስ አበባ፣ ኤማይ ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

*መንግስቱ ለማ*፡፡(1955*)፡፡ የግጥም ጉባኤ*፡፡አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሣህሉ አክሊሉና ሌሎች፡፡ (1993)፡፡ *የሥነጽሑፍ ዓይነቶች*፡፡ አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስትር፡፡

ባይ *ይማም* (2002)፡፡አጭርና ቀላል የአማርኛ ስዋስው፡፡አዲሰ አበባ፣አልፋ አሳታሚዎች፡፡

አገኘሁ አለማየሁና ሌሎች (1993)፡፡የድርሰት አጻጻፍ፣ አዲስ አበባ፣ትምህርት ሚኒስትር፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(2007)፡፡*የሥነጽሁፍ መሠረታውያን*፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ *ማተሚያ* ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993) ፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ *ማተሚያ* ቤት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1989)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ስዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

ደበበ ሰይፉ፡፡ (1980)፡፡ *የብርሃን ፍቅር፡፡* አዲስ አበባ፣ ቦሌ *ማተሚያ* ቤት፡፡

# ሙዳዩ ቃላት

ሙስና - ህጋዊ ያልሆነ ጥቅም ማግኘት

ወላጅ አጥ - እናት አባት በተለያዩ ምክንያቶች የተለዩአቸው

መደብ - የአመለካከት ጎራ/ፖለቲካ

ሳልስ - ሦስተኛ ፊደል

ሳድስ - ስድስተኛ ፊደል

ሚና - ድርሻ

የምልክት ቋንቋ - የአካላዊ እንቅስቃሴ ቋንቋ

መስማት የተሳናቸው - የማዳመጥ ችግር ያለባቸው

ክራንች - የእግር ችግር ያለባቸው መደገፊያ

ብሬል - የአይነ ስውራን መፃፊያ ገበታ

ዊልቸር - አካል ጉዳተኞች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ጋሪ

ጥገኛ - እራሱን ችሎ የማይቆም

ቅድመ - በመጀመሪያ

ድህረ - በስተ መጨረሻ

ስዋስው - አገባብ

ኃይለቃል - በአንቀጽ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የሚይዘው ዓረፍተ ነገር

ግጭት - አለመግባባት

ማዋቀር - ማደራጀት

እሬቻ - የኦሮሞ ባህላዊ በአል

ደራሮ - የጌዴኦ ዘመን መለወጫ

ጊፋታ - የወላይታ ዘመን መለወጫ

ፍቼ - የሲዳማ ዘመን መለወጫ

ጋዜ ማስቃላ - የጎፋ ዘመን መለወጫ

ዮዮ ማስቃላ - የጋሞ ዘመን መለወጫ

ያሆዴ ማስቃላ - የሀድያ ዘመን መለወጫ

ያሆ መሳላ - የከምባታ ዘመን መለወጫ

ያኦ ማስቃላ - የኦይዳ ዘመን መለወጫ

እርጥብ ሳር - የሰላም ምልክት / የእርቅ ምልክት

ጥንድ - ሁለት

ስልት - ዘዴ

ማስክ- በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታን ለመከላከል
የሚጠቅም የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ

ማጣመር - ማያያዝ /ማገናኘት

ኮሮና ቫይረስ - ወደ ሰው የሚተላለፍ ገዳይ በሽታ

ኤምኤ - ሁለተኛ ድግሪ

ፒኤችዲ - ሦስተኛ ድግሪ ወይም ዶክትሬት

ጠባብ - አስፍቶ የማይመለከት ፣ራስወዳድ

ጫፍ የወጣ - በአመለካከት መንገዱን የሳተ

የሀገር ፍቅር - አገርን መውደድ

መቻቻል - በትዕግስት መኖር / ተከባብሮ መኖር

የኑሮ ዘይቤ - የአኗኗር ሁኔታ

ችግር ፍቺ - መፍትሔ ሰጪ

ሳኒታይዘር - ንጽህና መጠበቂያ

ፈጠራ - ግኝት

መንስኤ - መነሻ ምክንያት

የባህል መድሐኒት - በባህላዊ መንገድ የተዘጋጀ መድሐኒት

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# 6ኛ ክፍል

# መርሐ ትምህርት

## ምዕራፍ አንድ

### መረዳት (ክፍለ ጊዜ 9 )

**የሚጠብቅ አጠቃላይ ውጤት** ፡- ተማሪዎቸ ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- በመጣመራቸው ምክንያት ተጨማሪ ፍች የሚያመጡ ቃላትን ፍች አዳምጠው ይመልሳሉ፤የሚና ጫወታዎችን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፤ ሳልስና ሳድስ ፊደሎችን አውቀው ቃላትን በትክክል ያነባሉ፤ ስርአተ ነጥቦችን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ ፤ ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ የሚሰጡ መሳሪያዎችን ስም ይዘረዝራሉ፤ ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን በመነጠል ያወጣሉ፡፡

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት (ክሂሎች)ስዋስው ሥነ-ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር -ማስተማር ክንውንና መረጃ መሳሪያዎች |
| --- | --- | --- | --- |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መረዳዳት | -ቃላትን ማጣመርና የጥምር ቃላትን ፍች መናገር<br><br>-አካል ጉዳተኞች የሚገለገሉባቸውን መሣሪያዎች ስም ማወቅ<br><br>- ጭውውትና የሚና ጨወታ<br>-ሳልስናሳድስ ፊደላትን ማንበብ<br>- የምንባቡን መልዕክት መረዳት<br>- ሥርዓተ ነጥቦች<br>- ቅጥያ<br>- እንቆቅልሽ | -በመጣመራቸው ምክንያት ተጨማሪ ፍች የሚያመጡ ቃላትን አዳምጦ መመለስ<br><br>-አካልጉዳተኞች የሚገለገሉባቸውን መሣሪያዎች ስም ማወቅ<br><br>-የተለያዩ ጫወታዎችን በመጫወት ሀሳባቸውን መግለጽ<br>-ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በትክክል ማንበብ<br>- የምንባቡን መልእክት ተረድቶ መናገር<br>- የሥርአተ ነጥቦችን ምንነት ማወቅና ዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል መጠቀም<br>-ስለ ቅጥያ ምንነት አውቀው ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን ለይቶ ማውጣት<br>-የእንቆቅልሹን ምንነት አውቀው የተለያዩ እንቆቅልሾችን መመለስ | ጥምር ቃላትን ማዳመጥ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎችን በማስታወሻ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠውን አጭር ሃሳብ ..ቀድመው እንዲያነቡ ማድረግ በመቀጠልም መምህሩ ቃላቱን ሲጠሩላቸው አዳምጠው ፍቺውን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br><br>- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የቀረበውን ስዕል እንዲመለከቱት ማድረግ ፣በስዕሉ ላይ ስላሉት መሳሪያዎች ስም እንዲናገሩ ማድረግ እና ከዚያም ግብረመልስ በመስጠት ማስተማር፡፡<br>- በጽሁፉ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በመጠየቅ፣ በመናገር እንዲመልሱ በማድረግ ማስተማር፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | -በመጀመሪያ ሳልስና ሳድስ ፊደላትን ጽፈው እንዲያነቡ ያለማምዷቸው በመቀጠልም የተዘጋጀውን ምንባብ ድምጽ አሰምተው እንዲያነቡ ማድረግ<br>- ይህንን ምንባብ ሲያነቡ ቅድመ ምንባብ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ዘዴን ተጠቅመው ማስተማር<br>- ቃላትን ሲያስተምሩ በመጀመሪያ በጥንድ ማደራጀትና የክፍል ስራውን ሰርተው እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>- በመጀመሪያም የስርዓተ ነጥቦችን አገልግሎት መንገር ከዚያም በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገቡበትን ቦታ ማሳየት<br>- በመቀጠልም የክፍል ስራውን ማሰራት<br>- በመጀመሪያ ተማሪዎች ማስታወሻውን እንዲያነቡት ማድረግ ቀጥሎ ስለ ቅጥያ የቀረበውን ተግባር ማሰራት<br>- ስለ እንቆቅልሽ ምንነት መንገር በመጀመሪያ አንድ እንቆቅልሽ አቅርቦ<br>ማሳየትና በቀጣይ እነሱ እንዲጫወቱ እድል መስጠት |

**መረጃ መሳሪያ**

- ጌታሁን አማረ (1984) የአማርኛ ሰዋስው መጸሐፍን
- ከይዘቱ ጋር የሚጣጣሙ ስዕሎች

**ግምገማ**

- በቃል ቃላትን አጣምሮ በመመስረት ፋቻቸውን እንዲናገሩ
- ማድረግ ፧
- አካል ጉዳተኞችን የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች ስም
- ዝርዝራቸውን መናገር፧
- የተለያዩ ጨዋታዎችን በመጫወት ሀሳባቸውን እንዲገለጽ
- ማድረግ ፧
- ሳልስና ሳድስ ፊደላትን በምንባቡ ውስጥ ጠንቅቀው
- እንዴት እንደሚያነቡ ማረጋገጥ፧
- አንብቦ የመረዳት ዘዴን በተግባር ማዋላቸውን ማረጋገጥ ፧
- ስርአተ ነጥቦችን አውቀው በአረፍተ ነገር ውስጥ

በትክክል መጠቀማቸውን ማረጋገጥ ፧

- ከቃላት ላይ ቅድመ ቅጥያንና ድህረ ቅጥያን ለይተው እንዲያዩ

ማድረግ

- በተማሩት እንቆቅልሽ መሰረት እንቆቅልሽ ሲጠይቁና ሲመልሱ
- ማየትና ማረጋገጥ ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### ባህላዊ የግጭት አፈታት (ክፍለ ጊዜ 9)

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የጓደኞቻቸውን ሀሳብ አዳምጠው ይረዳሉ ፣በሚሰጣቸው ርዕስ ላይ የቡድን ውይይት ያደርጋሉ፣ መመሪያዎችና ትእዛዞችን አንብበው ተግባራትን ይጽፋሉ፣ አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አንቀጽ መፃፍ ይችላሉ፣በየባህሉ ያሉ ባህላዊ እሴቶች የሚጠሩበትን ስያሜ መዝግበው ያቀርባሉ፣ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽን በቀላል አረፍተ ነገር ውስጥ እንዴት እንደሚዋቀሩ ያውቃሉ፤ቀለል ያለ ታሪኮችን አንብበው ይረዳሉ፡፡

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት(ክህሎት) ሰዋሰውና ስነ ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውንና መርጃ መሳሪያ |
|---|---|---|---|
| በህላዊ የግጭት አፈታት | - ባህል ነክ ቃላት<br>- ስዕሎችን ማወዳደርና መነፃፀር | - ባህል ነክ ቃላትን መለየት<br>- ስዕሎችን በመመልክት | - ባህላዊ ክንዋኔ የሚገለጹ ቃላት ቀርበዋል እነዚህ ቃላት በየትኛው ባህላዊ ክንዋኔ ጥቅም ላይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | - የአቻ ንግግር<br>- የምንባብ መልዕክት መረዳት<br>- መመሪያዎችና ትዕዛዞች<br>- አያያዥ ቃላት<br>- ባለቤት ፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ<br>- የቡድን ውይይት<br>- አፈታሪክ | በማወዳደርና በማነፃፀር ማብራሪያ መስጠት<br>- የጓደኞቻቸውን ሃሳብ በማዳመጥ መልዕክቱን መረዳት<br>- -ከምንባቡ የተረዱትን መልዕክት<br>- መመሪያዎችና ትዕዛዞችን አንብቦ ተግባርን መፈፀም<br>- የአያያዥ ቃላት ምንነትን | እንደሚውሉ እንዲናገሩ ማድረግ<br>- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ስዕሉን እንዲመለከቱ ማድረግ ፣በስዕሉ ላይ የተገለፀው ነገር የሚያስተላልፈው መልዕክት ምን እንደሆነ እንዲገምቱ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት<br>- ንግግሩን እንዲያዳምጡ ማድረግና ጥንድ ጥንድ ሆነው ንግግር እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>- የቅድመ ንባብ ጥያቄን መጠየቅና ከምንባቡ የተረዱትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግ ግብረ መልስ መስጠት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አውቀው ነጠላ ዓረፍተ ነገር በአያያዥ ቃላት ማጣመር<br>- ባለቤት ፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽን ተጠቅመው ነጠላ አረፍተ ነገርን ማዋቀር | - መመሪያና ትእዛዝን ማንበብ የሚኖረውን ጠቀሜታና ባለማንበብ ደግሞ የሚመጣውን ጉዳት በምሳሌ በማሳደግፍ ማስተማር<br>- በመጀመሪያ የአያያዥ ቃላት ምንነትን፣ አያያዥ ቃላት የሚባሉትን ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | - የቡድን ውይይት ማድረግ<br>- የአፈታሪክን ምንነት ማወቅና አፈታሪኮችን እንደገና መናገር | ረግ፣አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ነጠላ ዓረፍተ ነገርን እንዴት እንደሚያዋቅሩ ማሳየትና መልመጃ መስጠት<br>- ስለ ባለቤት ፣ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ምንነት መናገር፣ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲያቀርቡ ማሳየት<br>- የቡድን ውይይት በማደረግ ጊዜ ሥርዓቱን መከተል እንዳለባቸው መንገር ፣በመቀጠል በሚሰጣቸው ርዕስ ሥርአት ጠብቀው እንዲወያዩ ማድረግ<br>- የአፈታሪክን ምንነት ይንገሯቸው ከዚህ በፊት የሰሙት አፈታሪክ ካለ እንዲናገሩ ማድረግ ፤አፈታሪኮችንም በቡድን በመሆን በመደራጀት ለክፍል አምጥተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ |

**መርጃ መሳሪያ**

**ሞዴል ዓረፍተነገሮች፡፡**

**ለማስተማሪያ የተዘጋጁ ስዕሎች፡፡**

**ግምገማ**

- ባህላዊ ክንዋኔን የሚገልጹ ቃላትን እንዲናገሩ ማድረግ ፣
- ስዕሉን ተመልክተው የተረዱትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግ ፣
- ጥንድ ጥንድ በመሆን የአቻ ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ ፣
- ከምንባቡ ያገኙትን መልዕክት መጠየቅ ፣
- መመሪያና ትዕዛዝን ማንበብ የሚኖረውን ጠቀሜታ መጠየቅ ፣
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር ማዋቀራቸውን ማረጋገጥ ፣
- ባለቤት፣ተሳቢ፣ማሰሪያ አንቀጽ ያለውን ዓረፍተ ነገር መመስረቻቸውን ማረጋገጥ ፣
- የውይይት መመሪያን ተከትለው ውይይት ማድረጋቸውን መከታተል፣
- ስለ አፈታሪክ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ ፣

## ምዕራፍ ሦስት

## የሴቶች ሚና (9 ክፍለጊዜ )

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት :,- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የክርክሮችንና የውይይቶችን ሀሳብ አዳምጠው ያብራራሉ፡፡ ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፤ውስብሰብ (ጠንካራ) ቃላትን በትክክል ያነባሉ ፤የእለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን ጽፈው ይይዛሉ ፤ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ፤ያዛምዳሉ፤ በአያያዥ ቃላት ድርብ ዓረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ ፤ ቀለል ያሉ ስነ ጽሁፋዊ ምንባቦችን አንብበው መልዕክቱን ይናገራሉ፡፡

| የቋን ቋ ማስተ | ይዘት (ክህሎት) ስዋስውናሥነ- | የክህሎት ብቃት | የመማር -ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| የሴቶ ች ሚና | ክርክርና ጭውውት<br>- ስዕልን ተመልክቶ መናገር<br>- የቃላት ዓውዳዊ ፍች<br>- የግል ታሪክ<br>- ዕለታዊ ማስታወሻ<br>- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት<br>- ነጠላና ድርብ አረፍተ ነገር | - ክርክርን አዳምጦ ክርክር ማቅረብ<br>- ስዕልን ተመልክቶ ስለስዕል መናገር<br>- ቃላትን ከገቡበት አውድ አንፃር አውቆ ፍች መስጠት<br>- የራሳቸውንም ሆነ የአንድን ግለሰብ የህይወት ታሪክ እንዴት በጽሁፍ መልክ እንደሚቀርብ ማወቅ<br>- እለታዊ | - በቡድን በማደራጀት ክርክር ወይም ጭውወት እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>- የቀረበውን ስዕል በቡድን በመሆን እንዲመለከቱ ማድረግና ስዕሉን እያነፃፀሩ እንዲናገሩ ማድረግ<br>- ቃላቱን ከገቡበት አውድ አንፃር ተረድተው ፍች እንዲሰጡ ማድረግ<br>- የቀረበውን የግል ታሪክ ያንቡላቸው ከዚያም እነሱ ደግመው እንዲያነቡ ያድርጉ የቀረበውን ጥያቄ እንዲሰሩ ያድርጓቸው<br>- በመጀመሪያ አንድ የተዘጋጀ ስዕላዊ ማስታወሻ ያንቡላቸው፣ በመቀጠልም የቀረበውን የተማሪ ዕለታዊ ማስታወሻ እንዲያነቡ ያድርጉና ጥያቄውን ያሰሯቸው፡፡<br>- በተለመደው መሰረት ተመሳሰይና ተቃራኒ ቃላትን እንዲያዛምዱ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | - ተረት<br>- አጭር ግጥም አያያዥ ቃላት | ማስታወሻን ጽፈው መያዝ<br>- ለተመሳሰይና ለተቃራኒ ቃላት ፍች በመስጠት ማዛመድ<br>- ነጠላና ድርብ አረፍተ ነገርን ለይተው መመስረትና በጽሁፋቸው ውስጥ መጠቀም<br>- | ያድርጉ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | -<br>- ተረቶች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ማወቅ<br>- አጫጭር ግጥሞችን በትክክል ማንበብና የያዙትን መልዕክት መረዳት<br>- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ቃላትን፣ ሀረጋትን ፣ ዓረፍተ ነገሮችን ማያያዝ | -<br>- ነጠላ ዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ሰርተው ያሳዩአቸው በመቀጠልም ድርብ አረፍተ ነገርን ሰርተው ያሳዩአቸው ፤በመጨረሻም እነሱ እንዲሰሩ ያድርጉ<br>- የቀረበውን ተረት ደጋግመው እንዲያነቡ በማድረግ መልዕክቱን እንዲረዱ ያድርጉና መልዕክቱን እንዲናገሩ ያድርጉ<br>- የቀረበውን አጭር ግጥም በደንብና በትክክል እንዲያነቡ ያድረጉ።<br>- አያያዥ ቃላትን በመጀመሪያ ያሳዩአቸው<br>- አገልግሎታቸውንም ይንገሯቸው ከዚያም አያይዘው ያሳዩአቸውና ይዘዟቸው።<br>- |

**መርጃ መሳሪያ**

የክርክር መመሪያ

የአያያዥ ቃላት ሰሌዳ

**ግምገማ**

- በተግባር ክርክር እንዲያቀርቡ በማድረግ መገምገም
- የቃል ጥያቄ በመጠየቅ
- ምልከታ በማድረግ
- የእለት ተዕለት ማስታወሻ እንዲጽፉ ማድረግ
- የጽሁፍ ፈተና
- የቃል ጥያቄ በመጠየቅ
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄ መጠየቅ

## ምዕራፍ አራት

**አካባቢያችን** **(ክፍለጊዜ 9)**

የሚጠብቅ አጠቃላይ ውጤት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የጭውውቱን ሀሳብ አዳምጠው ይረዳሉ፤ስለአንድ አካባቢ በዝርዝር ይናገራሉ፤ ገረፍ ገረፍ የንባብ ስልትን ተጠቅመው መረጃን ያሰባስባሉ፤ለምን እንዴት የሚሉትን ቃላት በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፤የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን ፍች ያውቃሉ። ያታን በአረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፤ምሳሌያዊ ንግግሮችን አምጥተው ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ፤ከቃላት ውስጥ ቅድመ ቅጥያና ድህረ ቅጥያን ነጥለው ያወጣሉ ፤ስርአተ ነጥቦችን በአረፍተ ነገር ውስጥ በትክክል ይጠቀማሉ፡፤

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት (ክህሎት) ስዋስውና .ሥነ-ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር -ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| አካባቢያችን | - ውይይት<br>- አካባቢ ጥበቃ<br>- ምንባብ<br>- መጠይቃዊ ቃላት<br>- የሚጠብቁና የሚላሉ | - ጭውውትን አዳምጦ መረዳት<br>- ስለአካባቢ ጥበቃ መናገር<br>- በፍጥነት በማንበብ መረጃን ለቅሞ ማውጣት<br>- መጠይቃዊ ቃላትን | - ጭውውቱን ማስደመጥና የጭውውቱን መልዕክት መጠየቅ ፤ጥንድ ጥንድ በመሆን ጭውውት እንዲያቀርቡ ማድረግ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቃላት<br>- አነስታይና ተባዕታይ ፆታ<br>- ምሳሌያዊ ንግግሮች<br>- ጥያቄዎች<br>- ሥርዓተ ነጥቦች | በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም<br>- የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትን ለይቶ ማውጣትና ፍችያቸውን መረዳት<br>- አነስታይና ተባዕታይ ፆታን ለይቶ መረዳት<br>- ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መረዳት<br>- ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ለይቶ ማውጣት<br>- የድርብ ሰረዝንና የሦስት ነጥብን ምንነትና አገልግሎት መናገር<br>- | - ስለ አካባቢ ጥበቃ መረጃ መስጠት፤ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያውቁት ነገር ካለ መጠየቅ<br>- ንባቡን በፍጥነት እንዲያነቡና (የምንባቡን) መልዕክት ከውስጡ ለቅመው እንዲያወጡ ማድርግ<br>- የመጠይቃዊ ቃላትን ምንነትና መጠይቃዊ ቃላትን እንዲለዩ ማድረግ ፤ከዚያም መጠይቃዊ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ እያስገቡ እንዲጠቀሙ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት<br>- ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የፍች ለውጥ እንደሚያመጡ (እንዲኖራቸው)ያሳውቋቸው፤ቃላቱን አጥብቀውና አላልተው ሲያነቡ የፍች ለውጥ እንዲመጣ ያደረገውን ድምጽ ለይተው እንዲያውቁ ማድረግ |
| | - | - | - ስለ አንስታይና ስለ ተባዕታይ ፆታ ምንነት መንገር ጥያቄዎችን በማዘጋጀት አንስታይ ፆታን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | እንዲለዩ በማድረግ ማለማመድ<br>- የምሳሌያዊ ንግግር ምንነቶችና የሚያስተላልፉትን መልዕክት መንገር ፤የሚያውቁትን ምሳሌያዊ ንግግር ከነመልዕክቱ እንዲናገሩ መጠየቅ<br>- ቅጥያዎች በቃል ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ መናገር፣ ቅጥያዎችን ከ ዋናው ቃል እንዲለዩ የተለያዩ ቃላቶችን መስጠትና ሲሰሩ መከታተል የስርዓተ ነጥቦችን ምንነትና አገልግሎት መንገር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ፣ስርአተ ነጥቦች በአረፍተ ነገር ውስጥ ወይም በጽሁፍ ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባር እንዲያውቁ ማድረግ፤ ዓረፍተ ነገርን ወይም ጽሁፍን በማዘጋጀት ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀማቸውን መፈተሽ |

**መርጃ መሳሪያ**

የስርዓተ ነጥቦች ስዕል

የአካባቢ ጥበቃ ስዕል

**ግምገማ**

- ጭውውቱን ካዳመጡ በኋላ ከጭውውቱ የተረዱትን መልዕክት መጠየቅ
- ስለ አካባቢ ጥበቃ ጠቀሜታ የተረዱትን እንዲናገሩ በማድረግ
- በፍጥነት በማንበብ መረጃን መያዝ እንደሚቻል በመጠየቅ
- መጠይቃዊ ቃላትን በትክክል መጠቀማቸውን በመከታተል
- ቃላት ጥብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚኖራቸውን ፍች እንዲናገሩ በማድረግ
- አነስታይና ተባዕታይ ፆታን ለይተው ማወቃቸውን መጠየቅ
- ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያስተላልፉትን መልዕከት በመጠየቅ
- ቅጥያዎች በቃል ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ መጠየቅና ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል እንዲለዩ በማድረግ
- ሥርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀማቸውን በመፍተሽ

## ምዕራፍ አምስት

**የግለሰብ የህይወት ታሪክ (ክፍለጊዜ 9)**

**የሚጠብቅ አጠቃላይ ውጤት ፤ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ከሌሎች ተማሪዎች ልምድ በማዳመጥ የራሳቸውን ልምድ ይናገራሉ፤ ስዕሎች ካርታዎችና ሰንጠረዦች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ይናገራሉ፤ጥልቅ የንባብ ስልትን በመጠቀም የንባቡን መልዕክት ያወጣሉ፤ዋናና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ይሰጣሉ፤የዓረፍተ ነገር ስልቶችን ያውቃሉ፤በዓረፍተ ነገር ውስጥ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ይጠቀማሉ፡፡**

| የቋንቋ ማስተማሪያ | ይዘት (ክህሎት) ሰዋስውና ሥነ-ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር -ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| የግለሰብ የህይወት ታሪክ | - ልምድ ማካፈል<br>- ስዕል ፣ካርታ ፣ግራፍ ገለጻ<br>- ስዕላዊ ገለፃ<br>- የግለሰብ የህይወት ታሪክ<br>- አንቀጽ<br>- የንባብ ስልቶች<br>- የአረፍተ ነገር ክፍሎች<br>- ፈሊጣዊ ንግግር<br>- የቃላት | - የታዋቂ ሰዎችን ልምድ ማስደመጥ<br>- ስዕሎችን ካርታዎችን ግራፎችን ተመልክቶ መልዕክቱን መግለጽ<br>- በስዕል ላይ የተመሰረተ ገለፃ ማድረግ<br>- የግለሰብ የህይወት ታሪክን አንብቦ መልዕክቱን መናገር<br>- አንቀጽ ጽፈው ከአንቀፁ ውስጥ ዋና አረፍት ነገርና ዝርዝር አረፍተ ነገርን ለይቶ ማውጣት<br>የቀረበውን ምንባብ በጥልቅ ንባብ ዘዴ በመጠቀም | - የታዋቂ ሰዎችን ልምድ ማስደመጥ አያይዞም ልምድን ማካፈል የሚኖረውን ጠቀሜታ መናገር፤ ተማሪዎችም ተራ በተራ እየተነሱ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ በማድረግ ከስዕል ፣ ከታሪክና ከግራፍ እንዴት መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ<br>መናገር ፣ቀጥሎም ተማሪዎቹ የተለያዩ ስንጠረዥችን፣ ካርታዎችን፣ አይተው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቀጥተኛ ፍቺ<br><br>- | ማንበብ<br><br>- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ማወቅ<br>- ለፈሊጣዊ ንግግር ፍች መስጠት<br>- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠት | መረጃ ሰብስበው እንዲመጡ በማድረግ<br>- ስዕሉን በትኩረት እንዲያዩት ማድረግና ከስዕሉ ያገኙትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግና ግብረ መልስ መስጥት<br>- ከግለሰብ የህይወትታሪክ በመነሳት ጥሩ ተሞክሮዎችን መውስድ እንደሚቻል መንገር<br>- በመጀመሪያ ስለ አንቀጽ ምንነት መናገር፣ በመቀጠልም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ከአንቀጽ ውስጥ ዋና አረፍተ ነገርና ዝርዝር አረፍተ ነገርን እየለዩ ማስተማር በተማሩት መሰረትም ከሚሰጣቸው አንቀጽ ወይም ጽሑፍ ውስጥ ዋና እና ዝርዝር ዓረፍተ ነገርን ለይተው እንዲያሳዩ በማድረግ ማስተማር<br>- የጥልቅ ንባባ አስፈላጊነትን መናገር /ጥልቅ ንባባ የምንጠቀመው መች እንደሆነ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | መንገር<br>- የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው እንዲያውቁ በማድረግ<br>- ስለ ፈሊጣዊ ንግግር ምንነት መናገር፤ የፈሊጣዊ ንግግሮች ፍቻቸውን መናገር እና ተማሪዎቹ የሚያውቁት ፈሊጣዊ ንግግር ካለ ከነፍቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ<br>ለቃላት ቀጥተኛ ፍች እንዲሰጡ በማድረግ |

**መርጃ መሳሪያ**

ሞዴል አንቀጽ

**ግምገማ -**ልምድ ማካፈል የሚኖረውን ጠቀሜታ በመጠየቅ

- ከስዕል ፣ ከካርታና ከግራፍ ያገኙትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግ
- ስዕልን ተመልክተው ያገኙትን መልዕክት እንዲገልፁ ማድረግ
- ከግለሰብ ህይወት ታሪክ ያገኙትን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ
- ከአንቀጽ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን እንዲለዩ ማድረግ
- የጥልቅ የንባብ ዘዴን ተጠቅመው እንዲያነቡ ማድረግ
- የዓረፍተ ነገር ክፍሎችን ለይተው ማወቃቸውን መፈተሽ

-ለሚጠየቁ ፈሊጣዊ ንግግሮች  ትክክለኛ መልስ መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡

- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠታቸውን ማረጋገጥ

## ምዕራፍ ስድስት

## አገር ወዳድነት (ከፍለጊዜ 9)

**የሚጠብቅ አጠቃላይ ውጤት ፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚቀርቡትን ምንባቦች አዳምጠው ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡ሀገር በቀል እውቀቶችን አምጥተው ለክፍል ይናገራሉ፣ምንባቡን አንብበው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ተረድተው ይናገራሉ፤የተማሩትን መመሪያ ተከትለው ደብዳቤ ይጽፋሉ ፤ቃላትን አዳምጠው ቀጥተኛ ፍችያቸውን በቃል ይናገራሉ፤የአረፍተ ነገሮችን ስልት አውቀው ዓረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ፤ የቀረበላቸውን ግጥም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ያነባሉ፡፡**

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት (ክህሎት) ሰዋሰውና ሥነ-ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር -ማስተማር ክንውንና |
|---|---|---|---|
| የሀገር ፍቅር ስሜት | - ማዳመጥ<br>- አዳምጦ መረዳት<br>- ሀገር በቀል እውቀት<br>- ምንባብ<br>- አንብቦ መረዳት<br>- የግል ደብዳቤ መፃፍ<br>- የቃላት ቀጥተኛ ፍች<br>- የዓረፍተ ነገር ስልቶች<br>- ግጥም<br>- ነፃ ምዕላድ<br>- መጠይቃዊ | - የሚቀርብላቸውን ምንባብ አዳምጠው መረዳትና ጥያቄዎችን መመለስ<br>- ሀገር በቀል የሆኑ እውቀቶችን አምጥተው ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>- የተለያዩ ምንባቦችን አንብበው መልዕክቱን ማውጣት<br>- የግል /የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ ጽፎ ማቅረብ<br>- የቃላትን ቀጥተኛ ፍች መናገር<br>- የዓረፍተ ነገር ስሌቶችን አውጥቶ ዓረፍተ ነገርን መመስረት | - የሚደመጥ ምንባብን በማቅረብ አዳምጠው የሚቀርቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ማድረግ<br>- በጽሁፉ ላይ የተገለፀውን ሀገር በቀል እውቀት በደንብ እንዲረዱ ማድረግና ተመሳሳይ እውቀቶችን አምጥተው ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>- ቅድመ ንባብ ፤የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ሂደት እንደተጠበቀ ሆኖ ምንባቡን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቃላት | - ግጥሞችን በትክክል ማንበብ<br>- ነፃ ምዕላዶችን ከጥገኛ ምዕላድ መለየት<br>- መጠይቃዊ ቃላትን በዓረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም | አንብበው ያንብቦ መረዳት ጥያቄውን እንዲመልሱ ማድረግ<br>- በሚቀርብላቸው ምሳሌ መሰረት የግል ደብዳቤ መመሪያን ተከትለው ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግ<br>- በመጀመሪያ ቃላትን በማቅረብ ቀጥተኛ ፍቺያቸውን ማሳየት ከዚያም እነሱ እንዲሰሩ ማድረግ<br>- ሞዴል አረፍተ ነገሮች በቻርት አዘጋጅቶ በማምጣት የዓረፍተ ነገር ስልቶችን ማስተማርና በዚያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | መሰረት ማሰራት<br>- በመጀመሪያ ግጥሙን በትክክለኛ የንባብ ስልት ማንበብና በደንብ እንዲያዳምጡ ማድረግ በመቀጠል ባዳመጡት መሰረት ተማሪዎቹ እንዲያነቡ ማበረታታት‹‹<br>- ስለ ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ ማስተማርና ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ ልዩነት ገለፃ ማድረግ በመቀጠል በምሳሌዎች መሰረት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | መስራት በምሳሌው መሰረት ነፃና ጥገኛ ምዕላድን እንዲለዩ ማድረግ፡፡<br>- የመጠይቃዊ ቃላትን አገልግሎት በክለሳ መልክ ማብራራት በመቀጠልም በዓረፍተ ነገር ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ማሳየትና በዚያ መሰረት በዓረፍተ ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙ ማበረታታት |

**መርጃ መሳሪያ**

የነጻና ጥገኛ ምዕላድ ሰሌዳ

**<u>ግምገማ</u>**

- አጭር ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የቤት ሥራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት
- የንባብ ፈተና መፈተን
- የግል ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግ
- የጽሁፍ ፈተና
- ቀጥተኛ ፍችን በቃል እንዲናገሩ በማድረግ
- ዓረፍተ ነገሮችን ጽፈው እንዲያሳዩ በማድረግ

## ምዕራፍ ሰባት

## ባህል (ክፍለ ጊዜ 9)

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን ያዳምጣሉ፣ ባህላዊ መረጃን ይናገራሉ፣ ምንባብ አንብበው ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይረዳሉ፣ የአንቀጽ ማስፋፊያውን ተጠቅመው አንቀጽ ይጽፋሉ፣ ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፣ የአረፍተ ነገር ስልቶችን ይረዳሉ፣ የግጥም አላባውያንን ያውቃሉ፡፡

| የቋንቋው ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት(ክህሎቶች) ሰዋሰውና ስነ ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማርና ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| ባህል | - የተቀረፁ ታሪኮች<br>- -ባህላዊ መረጃ<br>- ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት<br>- አንቀጽን ማስፋፋት<br>- የቃላት አገባባዊ ፍች<br>- ተወላጠ ስሞች<br>- የአረፍተ ነገር ስልቶች<br>- የግጥም | - በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን አድምጦ መመለስ<br>- ስለአንድ ባህል መረጃ ሰብስቦ ማቅረብ<br>- ስለባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት መረዳት<br>- የአንቀጽ | - በሞባይል የተቀረጸውን ታሪክ ከማስደመጥ በፊት ርዕሱን ነግረው የቅድመ ማደመጥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፣ በመቀጠልም ታሪኩን ማስደመጥ፣ በትክክል ማድመጣቸውን ካዳመጡ በኋላ (የድህረ ማድመጥ) ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡<br>- መጀመሪያ ስለ ባህል ምንነት ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠልም ባህላዊ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አላባውያን<br>- ምሳሌያዊ ንግግር | ማስፋፊያ ስልት በማነጻጸርና በማወዳደር መጻፍ<br>- ለቃላት ከአገባባቸው አንጻር ፍች መስጠት<br>- የተወላጠ ስሞችን አጠቃቀም ማወቅ<br>- የአረፍተ ነገር ስልቶችን አውቆ መጠቀም<br>- የስንኝና የሐረግን ምንነት ማወቅ<br>- ምሳሌያዊ ንግግሮችን እች መረዳት | መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ፍንጭ መስጠት ስለሰበሰቡት መረጃ እንዲናገሩ ማድረግ<br>- ስለ ባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት ምንነት መንገር፤ የምግብ አዘገጃጀትን ምን እንደሚመስል ከምን እንደተዘጋጀ መናገር፡፡ በመቀጠልም እነሱ የሚያውቁት ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት ካለ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>- በመጀመሪያ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶችን (ዘዴዎችን) መንገር በመቀጠልም በምሳሌ በማስረዳት ያስተምሯቸው፤ ከዚያም በማነጻጸርና በማወዳደር ስልት እንዲጽፉ ማድረግ ስለ ቃላት አገባባዊ ፍች ምንነት መናገር በመቀጠልም በጽሁፉ ውስጥ ወይም በዐረፍተነገር ውስጥ የቃላት አገባባዊ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ፍች ምን እንደሚመስል በምሳሌ ማሳየት፤ በመቀጠልም ባሳዩት ምሳሌ መሰረት መረጃዎችን መስጠትና መከታተል<br>- በመጀመሪያ የተወሳጠ ስምን ምንነትና አጠቃቀም መናገር፤ በመቀጠልም ተወሳጠ ስሞችን በስም ቦታ እየተኩ እንዲሰሩ ያድርጉ መስራታቸውንም ይከታተሉ፡፡<br>- መጀመሪያ ስለ ዐረፍተነገር ስልት ስለስሞች ምንነት ይናገሩ በመቀጠልም ትዕዛዛዊና አገናኝ ዐረፍተነገር እንዴት እንደሚመሰረት በምሳሌ ያሳዩዋቸው፡፡ የተለያዩ ዐረፍተነገሮችን በማዘጋጀት ትዕዛዛዊና አጋናኝ ዓዐረፍተነገሮችን ለይተው እንዲያወጡ ማድረግ<br>- በመጀመሪያ ስለ ስንኝና ሐረግ ምንነት መናገር፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ከዚያም ግጥም በማዘጋጀት ከግጥሙ ውስጥ ሐረግንና ስንኝን ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ<br>- ምሳሌያዊ ንግግሮችን በማሰባሰብ ፍችያቸውን መናገር |

*መርጃ መሣሪያ*

*ግምገማ*

ታሪኩን በትክክል ማዳመጣቸውን ለማወቅ ጥያቄ መጠየቅ

ባህላዊ መረጃን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል እንዲናገሩ ማድረግ

ስለባህላዊ ምግብ አዘገጃጀት እንዲናገሩ ማድረግ

የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅመው አንቀጽ መጻፋቸውን ማረጋገጥ

ለቃላት አገባባዊ ፍች በትክክል መስጠታቸውን መከታተል

ተወላጠ ስሞችን በትክክል ለይቶ ማወቃቸውን ማረጋገጥ

ትዕዛዛዊና አጋናኝ ዐረፍተነገሮችን መመስረታቸውን መከታተል

ከግጥም ውስጥ ሐረግና ስንኝን ለይቶ ማውጣታቸውን ማረጋገጥ

ለምሳሌያዊ ንግግር ፍች መስጠታቸውን መከታተል

## ምዕራፍ ስምንት

## መቻቻል (ክፍለጊዜ9)

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፦በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን አዳምጠው የባህሉን ጠንካራና ደካማ ጎን ይናገራሉ፤ ቀለል ስላሉ የመስክ ጉዞዎች መረጃ ሰብስበው ይናገራሉ፤ ገላጭ ምንባቦችን በማንበብ የንባብ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤ የድርሰት አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ፤ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን ፍች አውቀው ይለያሉ፤ አምስቱን የቃል ክፍሎች በትክክል ያውቃሉ፤ መቼትና ዋና ገጸ ባህሪያትን ከስነ ጽሁፍ ውስጥ ለይተው ያወጣሉ፡፡

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት (ቋንቋ) ሰዋሰውና ስነ ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| ተቻችሎ መኖር | - በሞባይል የተቀረጹ አገር በቀል ዕውቀቶች<br>- የመስክ ጉዞ<br>- ምንባብ (ተቻችሎ መኖር)<br>- የድርሰት ክፍሎች<br>- ድርሰት | - በሞባይል ተቀርጸው የሚወጡትን አገር በቀል ዕውቀቶች ማዳመጥ ችለው መገናኛ ብዙሀንን አዳምጠው መረዳት<br>- የመስክ ጉዞ | - በሞባይል የተቀረጹ ታሪኮችን ወይም ንግግሮችን በማምጣት ለክፍል ተማሪዎች ያሰሟቸው ከዚያም የቀረቡትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው<br>- የተወሰነ ቀለል ያለ የመስክ ጉዞ ያዘጋጁና ተማሪዎችን ይዘው ይሂዱ ከዚያም መረጃቸውን እንዲሰበስቡ ያድርጉ በመጨረሻም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መጻፍ<br>- እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች<br>- ስም<br>- ቅጽል<br>- የልቦለድ አላባውያን<br>- ገጸ ባሕሪ<br>- መቼት<br>- መስተዋድድ<br>- ተውሳከ ግስ<br>- ግስ<br>- ቀጥተኛ ፍች | በማድረግ መረጃ መሰብሰብ መቻል።<br>- የመቻቻልን ምንነት ከምንባቡ መረዳት<br>- የድርሰት ክፍሎችን አውቆ ድርሰት መጻፍ<br>- ለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላት ፍች መስጠት<br>- የስምና የቅጽልን ምንነትና አገባብ ማወቅ<br>- የልቦለድን አላባውያን ምንነት ማወቅ<br>- ገጸ ባህሪያትንና መቼትን ለይቶ ማውጣት<br>የመስተዋድድ ፤ | የሰበሰቡትን መረጃ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ።<br>- ቅድመ ንባብ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ እንደተጠበቀ ሆኖ ምንባቡን ያስነብቧቸው<br>- የድርሰት ክፍሎችን በመጻፍ ላይ በቀረበው መሰረት ማስተማርና ለመግቢያ ለሀተታና ለመደምደሚያ የሚሆኑ አንቀጾችን ያጽፉ።<br>- በተማሩት መሰረት ድርሰት ጽፈው እንዲያሳዩ ያድርጉ<br>- የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን ምንነት ክለሳ በማድረግ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ<br>- የስምና የቅጽልን ባህሪያትንና አገባብ በመጀመሪያ ይግለፁላቸው ከዚያም አገባባቸውን ያስተምሩ በምሳሌው መሰረት የክፍል ስራውን ያሰሩ<br>- የልቦለድ አላባውያን ምን እንደሆኑ ይግለፁላቸው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የተውሳከ ግስና ግስ ምንነትና ተግባር አውቆ መጠቀም<br>- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠት<br>- | በመቀጠልም ስለ ገጸ ባህሪያትና ስለመቼት ያብራሩላቸው በመጨረሻም ከልቦለድ ውስጥ ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ<br>- የመስተዋድድን የተውሳከ ግስንና የግስን አገባብ በደንብ ይግለፁላቸው በመጨረሻም የክፍል ስራውን ያሰሩ<br>- ቀጥተኛ ፍች እንዲሰጡ ያድርጉ |

***<u>መርጃ መሣሪያ</u>***

**<u>-ቻርት</u>**

**<u>-ልቦለድ</u>**

**<u>ግምገማ</u>**

- ቃላዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ
- የጽሁፍ ፈተና
- የምንባብ ፈተና
- የተጻፉ ድርሰቶችን መገምገም
- የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን ፍች እንዲያወጡ በማድረግ
- ከስነ ጽሁፍ ውስጥ ገጸባህሪያትን እንዲያወጡ ማድረግ

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ተላላፊ በሽታዎች(ክፍለ ጊዜ 9)

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ ፡- የሚቀርብላቸውን ጥያቄ አዳምጠው ይመልሳሉ፤ ኮሮና ቫይረስ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ያብራራሉ፤ተራኪ ምንባቦችን አንብበው ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤ ተራኪ የሆኑ ድርጊቶችን ይጽፋሉ፤ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይሰጣሉ፤የስርወ ቃላትን ምንነት ይረዳሉ፤ የልቦለድ አይነቶችን ለይተው ያውቃሉ፤ ስማዊ ሐረግ ይመሰርታሉ፡፡

| በቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | | | |
|---|---|---|---|
| ተላላፊ በሽታዎች | ▪ አዳምጦ ጥያቄ መመለስ<br>▪ ኮሮና ቫይረስ<br>▪ ኮሮና ቫይረስ የሚተላለፍባቸው መንገዶች<br>▪ ተራኪ ድርሰት<br>▪ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች<br>▪ ስረው ቃል | የሚቀርብላቸውን ጥያቄ አዳምጦ መመለስ<br>• የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን መግለጽ<br>• የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን አውቆ መናገር<br>• ተራኪ ድርሰትን መጻፍ<br>• ለቃላት | ▪ በመጀመሪያ የሚያዳምጡትን ነገር ለተማሪዎቹ ማቅረብ በትክክል ማዳመጣቸውን ለማወቅ ጥያቄ መጠየቅና ግብረ መልስ መስጠት<br>▪ በመጀመሪያ ስለ ኮሮና ቫይረስ አስከፊነት መናገር፤ በመቀጠልም የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን መናገር፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ▪ የልቦለድ አይነቶች<br>▪ ስማዊ ሀረግ<br>▪ ግጥም | እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መስጠት<br>• ስለ ስርወ ቃል ምንነት ማወቅ<br>• የልቦለድ አይነቶችን ለይቶ ማወቅ<br>• ስማዊ ሐረግን መመስረት<br>• የግጥሙን ስንኝና ሐረግ ቆጥሮ ማውጣት | እንዴት መጠንቀቅ እንዳለባቸው የጥንቃቄ መንገዶቹን ይናገሩ።<br>▪ በኮሮና ቫይረስ የተያዘ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት መናገር<br>▪ በመጀመሪያ የተራኪ ድርሰትን ምንነት መናገር፤ በምሳሌ በማስደገፍ የተራኪ ድርሰት አጻጻፍን ማሳየት በመቀጠልም ድርሰትን ጽፈው እንዲያሳዩ ማድረግና ግብረ መልስ መስጠት<br>▪ ስለእማሬያዊ ና ፍካሬያዊ ቃላት ምንነት መናገር ከዚያም የተለያዩ ቃላቶችን በመስጠት እማሬያዊና ፍከሬያዊ ፍች እንዲሰጡ ማድረግ፤ በትክክል መስራታቸውን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ማረጋገጥ<br>▪ ስለ ስርወ ቃል ምንነት መናገር፤ ከቃል ውስጥ ስርወ ቃልን እየለዩ መናገር፤ በመቀጠልም ጥያቄዎችን መስጠት<br>▪ በመጀመሪያ ስለ ልቦለድ ምንነትና የልቦለድ አይነቶችን መናገር፤ በአጭርና ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያለውን አንድነትና ልዩነት መናገር፤ የስማዊ ሐረግ ምንነትን መናገር በመቀጠልም ስማዊ ሐረግ እንዴት እንደሚመሰረት ማሳየት፤ በተማሩት መሰረት ሐረጉን መመስረታቸውን መከታተል<br>▪ የግጥሙን ስንኝና ሐረግ እየቆጠሩ ማሳየት |

## መርጃ መሣሪያ

### ግምገማ

- የሚደመጠውን ነገር በማቅረብ
- ስለኮሮና ቫይረስ አስከፊነት እንዲናገሩ በማድረግ
- የኮሮና ቫይረስ መተላለፊያ መንገዶችን መናገር
- ድርሰት እንዲጻፉ ማድረግና መገምገም
- ለእማሬያዊና ለፍካሬያዊ ቃል ፍች እንዲሰጡ በማድረግ
- ከቃል ውስጥ ስርወ ቃልን እንዲለዩ በማድረግ
- የልቦለድ አይነቶችን እንዲለዩ በማድረግ
- ስማዊ ሐረግን እንዲመሰርቱ በማድረግ
- ከግጥም ውስጥ ስንኝና ሐረግ ቆጥሮ እንዲያወጡ በማድረግ

# ምዕራፍ አሥር

የፈጠራ ስራ(ክፍለ ጊዜ 9)

የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ፡- የፈጠራ ስራዎችን አዳምጠው ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፤ ለማህበራዊ አውዶች ሀሳብን በአክብሮት ይገልጻሉ፣ ከምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይረዳሉ፣ ገላጭ ድርሰት መጻፍ ይችላሉ፣ ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም ይሰጣሉ፣ ግሳዊ ሀረግን ያውቃሉ፣ አነጻጸሪ ዘይቤን ምንነት ይረዳሉ።

| የቋንቋ ማስተማሪያ ርዕስ | ይዘት (ክፍሎች) ሰዋስውና ስነ ጽሁፍ | የክህሎት ብቃት | የመማሪያ ማስተማር ክንውን |
|---|---|---|---|
| የፈጠራ ስራ | ▪ ማዳመጥ<br>▪ የአክብሮት (የትህትና) ንግግር<br>▪ የምንባቡን መልዕክት መረዳት<br>▪ ገላጭ ድርሰት<br>▪ የቃላት ተዛማጅ ትርጉም<br>▪ ስዕልን ተመልክቶ መረዳት<br>▪ ግሳዊ ሐረግ<br>▪ ቅጽል | ▪ ስለፈጠራ ስራ የቀረበውን ምንባብ ማዳመጥ<br>▪ የአክብሮት ንግግርን አውድ መተግበር<br>▪ ካነበቡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት መናገር<br>▪ ገላጭ ድርሰትን መጻፍ<br>▪ ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም መስጠት | ▪ በመጀመሪያ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ በመቀጠልም ምንባቡን በማንበብ እንዲያዳምጡ ማድረግ በትክክል ማዳመጣቸውን በማረጋገጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ (የተረዱትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግ)<br>▪ በመጀመሪያ የአክብሮት (የትህትና) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ▪ ዘይቤ | ▪ ስዕሎችን በመመልከት ማብራራት<br>▪ ግሳዊ ሀረግ መመስረት<br>▪ ቅጽሎችን ወደ ብዙ ቁጥር መቀየር<br>▪ ስለ አነጻጸሪ ዘይቤ መናገር | ንግግር ምን እንደሆነ መናገር፡፡ በመቀጠልም አውድን ተጠቅመው ተገቢውን ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ<br>▪ ከምንባቡ ውስጥ የተረዱትን መልዕክት እንዲናገሩ ማድረግ<br>▪ በመጀመሪያ ስለ ገላጭ ድርሰት ምንነት መናገር፣ በመቀጠልም አንድ ርዕስ መርጠው አንድ ገላጭ አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ<br>▪ ስለቃላት ተዛማጅ ትርጉም ምንነት እንዲናገሩ ማድረግ፣ በመቀጠልም ተዛማጅ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በመለየት እንዲሰሩ ማድረግ<br>▪ ስዕሎችን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | እያዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግ፣ ስዕሎቹን በማነጻጸር ስለምን እንደሚያወሩ እንዲናገሩ ማድረግ<br>▪ በመጀመሪያ ስለግሳዊ ሐረግ ምንነት መናገር ከዚያም ሀረጉን እየመሰረቱ ማሳየት፣ በተማሩት መሰረት ሀረጉን በትክክል መመስረታቸውን መከታተል፡፡<br>▪ ስለትጽላዊ ሐረግ ምንነት መናገር ከዚያም ቅጽሎችን ወደ ብዙ ቁጥር እየቀየሩ ማሳየት፣ ጥያቄዎችን መስጠት<br>▪ በመጀመሪያ ስለ ዘይቤ ምንነት ና አይነቶች መናገር፤ ከዚያም ስለ አነጻጻሪ ዘይቤ ምሳሌዎችን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | እየሰጡ ማሳየት፣ በተማሩት መሰረትም አነጻጸሪ ዘይቤን እንዲናገሩ ማድረግ |

***<u>መርጃ መሣሪያ</u>***

**-ቻርቶች**

***<u>ግምገማ</u>***

- የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን እንዲናገሩ በማድረግ
- የጥንድ ስራ በመስጠት
- የተረዱትን መልዕክት እንዲናገሩ በማድረግ
- አንድ ርዕስ መርጠው ገላጭ አንቀጽ እንዲፅፉ በማድረግ
- ለቃላት ተዛማጅ ትርጉም እንዲሰጡ በማድረግ
- ከስዕሉ የተረዱትን /የተገነዘቡትን/ ነገር እንዲገልፁ በማድረግ
- የሀረግ አይነቶችን በትክክል ለይተው ማወቃቸውን በመጠየቅ
- አነጻጸር ዘይቤን ለይተው ማወቃቸውን በመገምገም